# 10

# የደራሲውን ዓላማ መረዳት

አራተኛው አጠቃላይ መርህ ሁለት ነገሮችን ይሸፍናል፦ በጸሐፊው ዓላማና ዕቅድ መሠረት ትርጓሜ ይስጡ። እነዚህ ሁለቱ በጣም የተዛመዱ ስለሆኑ ልዩነታቸውን ልብ እያልን በአንድ ላይ ልናያቸው እንችላለን።

የጸሐፊው "ዓላማ" ማለት እንዲጽፍ ያነሣሣው በአእምሮው ያለው ጉዳይ ነው። ዮሐንስ "የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ...ይህን ጽፌላችኋለሁ" (1ኛ ዮሐ. 5፡13)፥ በማለት ሲጽፍ፥ ዓላማውን በግልጥ ያስረዳል። "ዕቅድ" ደራሲው ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ይረዳው ዘንድ ጽሑፉን የሚያዋቅርበት ስልት ነው። ለምሳሌ የኤፌሶን መጽሐፍ የሚታወቅበት ስልት አለው። የመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ስለ ክርስቲያን መጠራት ሲናገሩ፥ ተከታዮቹ ሦስት ምዕራፎች ደግሞ ክርስቲያን ሕይወቱን እንዴት እንደሚመራ ይናገራሉ። ይህን በምዕራፍ 4 መጀመሪያ ላይ ከሚገኘውና "እንግዲህ" ከሚለው ቃል በከፊል እንረዳለን።

ከላይ በተጠቀሱት ምሳሌዎች መሠረት ዓላማና ዕቅዶችን መመልከቱ ቀላል ነው፤ ይሁን እንጂ ሁልጊዜ ግልጥ አይደሉም። እንደውም በአብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ዓላማቸው ያልተገለጠ በመሆኑ ለመግር አዳጋቾች ናቸው። ብዙ ጊዜ የአንድ መጽሐፍ ዕቅድ ከዓላማው ይበልጥ ግልጥ ነው። የጸሐፊውን ዓላማና ዕቅድ ካላወቅን በአራተኛው መርህ ለመጠቀም አንችልም። ዓላማና ዕቅዱን ማግኘቱ ደግሞ አዳጋች በመሆኑና መርሁ ከሌሎች ጉዳዮች ይልቅ ከባድ በመሆኑ እምብዛም አንጠቀምበትም። ቢሆንም ጉዳዩ ጠቃሚ ነውና አጠቃቀሙን በተመለከተ አንዳንድ ምሳሌዎችን እናያለን።

## የደራሲው ዓላማ

ዮሐንስ ወንጌል ለመጻፍ የተነሣበትን ዓላማ፥ በመጽሐፉ ምዕራፍ 20፡31 ላይ፥ "ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል" በማለት ይገልጣል። የኢየሱስን ተአምራት የገለጠውም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን (ማንነቱን) ሰዎች እንዲያምኑና በዚያ እምነት አማካይነት የዘላለም ሕይወት (ደኅንነት) እንዲቀበሉ ነው። እዚህ ውስጥ የሚካተቱ ሦስት ታላላቅ እውነቶች አሉ፤ እነርሱም፦ የክርስቶስ ማንነት፥

እምነትና ሕይወት ናቸው። ዮሐንስ ስለ ምልክቶቹ የጻፈው፥ ሰዎች እነዚህን እውነቶች ይለማመዱ ዘንድ መሆኑን እራሱ ይናገራል።

ያን ተከትሎ እያንዳንዱ ተአምር ምናልባት ስለ ክርስቶስ ማንነት፥ ስለ እምነትና ሕይወት የተወሰነ ነገር ያሳይ ይሆናል። የእያንዳንዱን ተአምር ትርጉም ለመረዳት ስንፈልግ ይህን መዘንጋት የለብንም። ለምሳሌ በዮሐንስ 2፥1-11 የተጻፈውን የኢየሱስን የመጀመሪያ ምልክት ልንወስድ እንችላለን። ስለ ክርስቶስ ማንነት ምን ይገልጣል? በእርግጥ ፈጣሪና የፍጥረታት ሁሉ ገዥ መሆኑን ያስረዳል። ቁጥር 11 እንደሚያመለክተው ደቀ መዛሙርቱ የክርስቶስ ተአምራዊ ሥራዎች ክብሩን የገለጡ መሆኑንም ተገነዘቡ።

ምልክቱ ስለ መንፈሳዊ ሕይወትም አንዳንድ ነገሮችን ይገልጣል። በወይን ጠጅ ማለቅ እንደተጠቆመው ሁሉ፥ የሰው ዘር ሕልውና በውድቀት ተገለጠ። ነገር ግን ክርስቶስ የተሻለና የተትረፈረፈ ሕይወት ይሰጣል (“መልካሙን ወይን ጠጅ”)። ይህ ከክርስቶስ የሚገኝ ሕይወት እርካታና ሙላት ያለው መሆኑ ተመልክቷል።

እዚህ ላይ ስለ እምነትም የተሰጠ ትምህርት አለ። የማርያም እምነት፥ ማለትም በክርስቶስ የነበራት ሙሉ እርግጠኛነት ቁጥር 5 ላይ “የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ” ብላ በተናገረችው ተመልክቷል። እምነትም ወደ መታዘዝ የሚመራ ስለሆነ ኢየሱስ ባዘዛቸው ጊዜ አገልጋዮቹ ታዘዙ። ኢየሱስ በዚያ እምነትና መታዘዝ ውስጥ በመሥራቱ ሰዎቹ ተአምራትን ተለማመዱ። ደቀ መዛሙርቱም ተለማመዱትና “በእርሱ አመኑ” (ቁ. 11)። እንግዲህ የዮሐንስን ዓላማ ማወቁ፥ የተአምራቱን መንፈሳዊ ዓላማ እንድናይ ይረዳናል።

## የደራሲው ዕቅድ

በጸሐፊው ዕቅድ መሠረት ትርጓሜ የመስጠት ምሳሌ በዘፍጥረት መጽሐፍ ሊገኝ ይችላል። አንድ ሰው ከዘፍጥረት መጽሐፍ (5፥1፤ 6፥9፤ 10፥1፤ 11፥10፥ 27፤ 25፥12፥ 19፤ 36፥1፥ 9፤ 37፥2) በጥንቃቄ በማንበብ “ልደቱ፥ ወይም ትውልዱ ይህ ነው” የሚሉትን ሐረጎች መደጋገም ልብ ይላል። ስለዚህ የሐረጉ ብዙ ጊዜ መደጋገም የአጋጣሚ ሊሆን አይችልም። ታዲያ ጠቀሜታው ምንድነው? መጽሐፉን ለመገንዘብስ ይህ እንዴት ሊረዳን ይችላል? የሐረጉን ኃይል ለማየት ይረዳዎ ዘንድ ከእያንዳንዱ ድርጊት ጋር ተዛማጅ የሆኑ እውነቶችን በአምድ እየዘረዘሩ ይመዝግቧቸው፦ የተጠቀሰውን ሰው፥ የምንባቡን ይዘት (ማለትም የዘር ሐረግ፥ የግል ታሪክ፥ ወዘተ.) እና የምንባቡን ስፋት።

ጥናትዎን እንዲህ ሲቀጥሉ የተለያዩ እውነታዎች ግልጥ ይሆ ኑልዎታል። ለምሳሌ የዘፍጥረት መጽሐፍ ሁለት ክፍል አለው፤ የመጀመሪያው እስከ አብርሃም ያለው ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ስለ አብርሃምና ከእርሱም በኋላ ስለሚመጡት አባቶች ይናገራል። የመጀመሪያው ክፍል በአብዛኛው የትውልድ ሐረግን ታሪክ የሚዘረዝር ሲሆን፥ ሁለተኛው የግለሰቦችን ታሪክ ይናገራል። መላው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በዘራው "ዘር" ወይም መሥመር የሚሠራውን ዕቅድ ይናገራል። እግዚአብሔር ስለ እስማኤልና ኤሳው በግል የሚገደው ቢሆንም፥ እነሱ በዓላማው መሥመር ውስጥ ያለመሆናቸውን ነው መጽሐፉ የሚገልጠው። አብርሃምና ያዕቆብ ከባድ መንፈሳዊ ድካም ቢኖርባቸውም፥ እግዚአብሔር ለዓላማው የመረጣቸው ስለሆኑ፥ በመጽሐፉ ውስጥ ሰፊ ስፍራ ተሰጥቷቸዋል።

እንግዲህ የአንድን መጽሐፍ የተለያዩ ምንባቦች የምንተረጉመው፥ በመጽሐፉ ዓላማና ዕቅድ መሠረት ነው። የዮሐንስ ወንጌል ዓላማና የዘፍጥረት መጽሐፍ ዕቅድ ለዚህ መልካም ምሳሌዎች ናቸው።

## ዓላማና ዕቅድን ማግኘት

ዋናው ጥያቄ የጸሐፊውን ዓላማና ዕቅድ ልናውቅ (ልናገኝ) እንችላለን? የሚለው ነው። አንዳንድ አሳቦች እነሆ፡-

1. *ዓላማው በጽሑፉ ውስጥ በግልጥ መቀመጥ ያለመቀመጡን ያስተውሉ።* ዓላማው ግልጥ ካልሆነ፥ ይህን የሚያመለክቱ ሁኔታዎች ወይም ፍንጮች አሉ? ለምሳሌ፥ ጳውሎስ በሁለቱም የቆሮንቶስ መልእክቶቹ በአንድም ስፍራ ዓላማውን በግልጥ አላስቀመጠም። ሆኖም በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡11፤ 3፡4፤ 4፡6-7፤ 7፡1፥ 18፤ 8፡1፤ 12፡1፤ 16፡1፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 2፡3-4፤ 7፡5-8፥ 10-13 ያሉትን ክፍሎች በማነጻጸር ዓላማውን ለማግኘት እንችላለን። ከነዚህ ክፍሎች ልንማር የምንችለው ቁም ነገር አንዳንድ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች (ክርስቲያኖች) ለጳውሎስ ስለ ቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን መልካም ያልሆነ ወሬ ያመጡለት መሆኑን ነው። በቡድን መለያየት፥ መካሰስ፥ ምግባረ ብልሹነት፥ በጌታ እራት ጊዜ ሥርዓት ማጣት ታይተዋል። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሌሎች እንደበተ ርቱዕ ተናጋሪዎች ስለነበሩ፥ አንዳንድ ሰዎች የጳውሎስን የሐዋርያነት ሥልጣን ይቃወሙ ነበር። እንዲሁም የቆሮንቶስ ሰዎች አንዳንድ ጥያቄዎችን በማንሣት ለጳውሎስ ደብዳቤ ጻፉለት። እርሱም ራሱን አጥብቆ በመግለጥ መልስ ሰጣቸው (1ኛ ቆሮንቶስ)፤ ሆኖም ይህ ጠንካራ መልስ መንፈሳቸውን ይጎዳዋል ብሎ ፈራ። የቆሮንቶስ ሰዎች መልእክቱን በደህና ሁኔታ

የተቀበሉት መሆኑን ቲቶ ሲነግረው፥ ጳውሎስ ለዚህ እግዚአብሔርን እንዳመሰገነ በመግለጥና ከሐሰተኛ ሐዋርያት እንዲጠበቁ በማስጠንቀቅ እንደገና (2ኛ ቆሮንቶስን) ጻፈላቸው። ከነዚህ እውነታዎች በመነሣት ጳውሎስ እያንዳንዱን ደብዳቤ የጻፈበትን ዓላማ ለመገመት እንችላለን።

ያም ቢሆን ከፍንጭ በመነሣት ብቻ ከመወሰን ይጠንቀቁ። ፍንጮች ቢኖሩ እንኳን ዓላማውን በግልጥ የሚያመለክቱ መሆን አለባቸው። ግልጥ ያልሆኑ ሐረጎችን መሠረት በማድረግ ዓላማውን ለማግኘት መገመት መልካም አይደለም። አንድን መጽሐፍ ለመረዳት የግድ ዓላማውን ማወቅ አለብን ማለትም አይደለም። ሆኖም የዓላማው ግልጥ መሆን መጽሐፉን በሚገባ ለመረዳት ያስችለናል።

2. *ለአንባቢዎች በግል የሚሰጡ ማገናዘቢያዎች ብዙ ጊዜ የመጽሐፉን ዓላማ ያመለክታሉ።* የተደጋገሙ ወይም ትኩረት የተሰጣቸው ጭብጦች ወይም መሠረተ አሳቦችም ይህን ሊጠቁሙ ይችላሉ። ማቴዎስ ስለ መንግሥተ ሰማይ እውነታ ብዙ ጊዜ ስለሚያነሣ፥ ወንጌሉን ቢያንስ በከፊል ለዚህ ዓላማ እንደጻፈው እርግጥ ነው።

3. *የመጽሐፉን አወቃቀር ወይም አደረጃጀት ይፈልጉ።* እንደ ሮሜ 12፡1 እና ኤፌሶን 4፡1 ባሉት ጥቅሶች እንደሚታየው ግልጥ የክፍፍል ነጥቦች ሊኖሩ ይችላሉ። በዘፍጥረት መጽሐፍ እንደታየው የተደጋገሙ ቃላት ወይም ሐረጎች ይኖሩ ይሆናል። ነገር ግን እዚህም ጥንቃቄ ያሻል። "ሰማያዊ ስፍራ" ወይም "ሰማያት" የሚል ሐረግ በኤፌሶን መጽሐፍ አምስት ጊዜ ቢጠቀስም፥ የመጽሐፉን ክፍፍል ግን አያመለክትም። ስለሆነም እንዲያው በግምት አይጠቀሙ።

4. *ዓላማውና ዕቅዱ ወይም ከሁለቱ አንዱ ግልጥ ከሆኑልዎ ትርጓሜዎ ከዚሁ ጋር እንደሚስማማ እርግጠኛ በመሆንና ይህን፥ በአእምሮዎ በመያዝ፥ እያንዳንዱን የመጽሐፉ ክፍሎች ያጥኑ።*

ከላይ የተጠቀሱትን አሳቦች በአእምሯችን በመያዝ አንድ ሌላ ምንባብ እንመልከት። ፊልጵስዩስ 2፡1-8 የጸሐፊውን ዓላማ የሚያሳይ ምንባብ ነው። "አንድ አሳብ"፥ "አንድ ፍቅር" እና "አንድም ልብ" የሚሉት ሐረጎች ጳውሎስ ስለ ፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች የኅብረት ደረጃ መጨነቁን ያሳያሉ። በመሆኑም ከቁጥር 5-8 ባለው ክፍል የክርስቶስን ምሳሌነት ያስታውሳቸዋል።

ክርስቶስ ግልጥ ወይም እርግጠኛ አሳብ ነበረውና ተግባሩን በእርግጠኛነት አከናወነ። ከእግዚአብሔር ጋር እኩል ለመሆን አልጣረም (ቁ. 6)። ራሱን ባዶ አደረገ (ቁ. 7)፥ ከዚያም ይልቅ አሳፋሪ እስከሆነው

የመስቀል ሞት ራሱን ዝቅ አደረገ (ቁ. 8)። በመሆኑም የክርስቶስ ሞት የትሕትና ምሳሌ ነው። የክርስቶስ ሞት ሌሎች ብዙ ምንባቦች እንደሚያስተምሩን የእግዚአብሔርን ፍቅር ወይም ለኃጢአታችን ቤዛ መሆኑን ማሳየት አይደለም። ይህ አይደለም ነጥቡ። የደራሲው ዓላማ ትኩረቱን በየምንባቡ ይመራል ወይም ያመለክታል።

አራተኛውን አጠቃላይ የትርጓሜ መርህ እንዲጠቀሙበት የሚያስችሉዎ አንዳንድ ምንባቦች እነሆ፡-

በምሳሌ 1፡1-6 ላይ የተገለጠው ዓላማ በሌሎቹ ምንባቦች ትርጉም ላይ እንዴት ነው ተጽዕኖ የሚያደርገው?

በመጽሐፈ መክብብ፡- "ከፀሐይ በታች" የሚለው ሐረግ ለዚህ መጽሐፍ ቁልፍ ይሆን ይሆናል። ይህን ማወቁ እንደ 2፡17፥ 20፥ 24፤ 9፡4 ያሉትን አስቸጋሪ ጥቅሶች ለመረዳት ይረዳ ይሆን?

ሉቃስ 1፡1-4ን ያንብቡና በመጽሐፈ ምሳሌ የተጠቀሰውን ኃላፊነት ጥያቄ በዚህም ላይ ይመልሱ። በገላትያ 1 ላይ ጳውሎስ "የወንጌል" የሚለውን ቃል ከመደጋገሙና መልእክቱን በድንገት ከመጀመሩ (ምሥጋና ሳይሰጥ) አንጻር ይመልከቱት።

የቈላስይስን መጽሐፍ ለመጻፍ ጳውሎስ የነበረውን ዓላማ ስለሚያመለክቱ አስተያየቶች፡- ቈላስይስ 2፡4፥ 8፥ 16፥ 20፥ 22ን ይመልከቱ።

# 11

# ቅድመ ሁኔታውን ማጥናት

አምስተኛው አጠቃላይ መርህ፡- "ሊታወቅ እስከተቻለ ድረስ፥ በቀድሞው ታሪካዊ፥ መልክአ ምድራዊና ባህላዊ ሁኔታ መሠረት ትርጓሜ ይስጡ" የሚል ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ሁነቶች የተፈጸሙት በታሪክ በታወቁ ጊዜያት ነው። በዚያን ዘመን የኖሩትን ሰዎች፥ በተለይም በአብዛኛው የአይሁዶችን ባህል ተጋርቷል። አዲስ ኪዳን ከመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የፍልስጥኤም ባህልና ከዚያ ዘመን ቀድሞ ከነበረው ታሪክ ጋር ይገናኛል። አዲስ ኪዳንን በራሳችን ባህል መሠረት ከተረጎምነው በቀላሉ እንሳሳታለን።

አንድ ዓይነት ድርጊት፥ አባባል ወይም ሁኔታ በተለያዩ ባህሎች የተለያዩ ትርጉሞች እንደሚኖሯቸው ልብ ልንል ይገባል። ለምሳሌ፡- በእንግሊዝ አገር አንድ ሰው ስለ አንዲት ሴት ሲናገር "homely" ["ሆምሊ"] ያለ እንደሆነ፥ ውጭ ውጭ የማትልና ትዳርዋን የምትወድ መሆንዋን ስለሚገልጥ የተናጋሪውን አድናቆትና አክብሮት ያመለክታል። ይህ ቃል በአሜሪካ ስድብ ነው። በዚያ ባህል መሠረት ቃሉ አስቀያሚነትን ነው የሚገልጠው። በአንዳንድ የህንድ ክፍሎች አንድ ሰው "ጉጉት" ወይም "የጉጉት ልጅ" የተባለ እንደሆነ እንደ ስድብ ይቆጥረዋል። በአሜሪካ ግን የአድናቆት መግለጫ ነው። የቃሉ ትርጉም ለህንዳዊ "ደደብነትን" ሲያመለክት፥ ለአሜሪካዊው ግን "ጠቢብነትን (አስተዋይነትን)" ይገልጥለታል።

በአንድ ባህል ወይም ታሪክ በአንድ ወቅት ትርጉም ያለው አገላለጥ፥ ወይም ዘይቤ፥ በሌላው ምንም ትርጉም አይኖረው ይሆናል። ትርጉሞች ስለሚለዋወጡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባሎችን በባህላዊ አገባ ባቸው መረዳት ያስፈልገናል። በ2ኛ ነገሥት 2፡9 ኤልሳዕ የኤልያስን መንፈስ "ሁለት እጥፍ" ያገኝ ዘንድ ይጠይቃል። ይህን እኛ በራሳችን ባህል መሠረት ስናስበው ኤልሳዕ የፈለገው ኤልያስ የነበረውን መንፈስ (ምናልባት መንፈስ ቅዱስ) ሁለት እጥፍ ይመስለናል። ነገር ግን በእነዚህ ሁለት ሰዎች ባህላዊ ሁኔታ (በተለይም ዘዳግም 21፡17) መሠረት ኤልሳዕ የጠየቀው አንድ የበኩር ልጅ የሚገባውን ውርስ ይመስላል፤ የኤልያስ ወራሽ መሆን።

በመሆኑም የአንድ ምንባብ የመጀመሪያውና ቀዳሚው ትርጉም በዚያ ዘመን በነበረው ባህላዊና ታሪካዊ ሁኔታ መሠረት መሆኑን

ያስታውሱ። ያም በዚያን ዘመን ይኖሩ ለነበሩ ሰዎች ይሰጥ የነበረው ትርጉም ማለት ነው። በተቻለን መጠን ያን ትርጉም መረዳት ይኖርብናል፥ ቀዳሚው ጉዳይ ያ ነውና።

የዚህ መልካም ምሳሌ ሉቃስ 9፡23 ሲሆን፥ ይኸውም ኢየሱስ ሊከተለው የሚወድ ማንም ቢኖር "በየዕለቱ መስቀሉን ተሸክሞ" ከኋላው እንዲመጣ ከተናገራቸው ጥቅሶች አንዱ ነው። እኛ፥ መስቀላችንን መሸከም ማለት፥ መከራን ወይም ሥቃይን ወይም አስቸጋሪ ሰዎችን መቻል ማለት እንደሆነ እንናገራለን። ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ዘመን ግን መስቀሉን የሚሸከም ሰው በስቅለት ለመቀጣት በጉዞ ላይ ያለ ወንጀለኛ ነበር። ክርስቶስ ራሱም ወደ ሞት ሲሄድ መስቀሉን ተሸከመ። ስለሆነም በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች የኢየሱስን አባባል በዚያ ትርጉሙ ተረድተውታል። ኢየሱስ ይናገር የነበረው ስለ ሥጋዊ ሥቃይ ሳይሆን ስለ ሞት (ሥጋዊ ወይም መንፈሳዊ) እንደሆነ ተረድተዋል። በወንጌሎች፥ በተለይም፥ የኢየሱስን ሞት በሚናገሩ ሌሎች ምንባቦች ውስጥ ይህ ትርጉም ግልጥ ተደርጓል። እኛ ትርጓሜ ልንሰጠው የሚገባ በዚያ ትርጉሙ መሠረት ብቻ ነው።

የሁሉንም ምንባቦች የመጀመሪያ ትርጉም ለማግኘት እንደማይቻል እንረዳለን። እንደ ዕድል ሆኖ ብዙም ባይሆኑ፥ ዘጸአት 28፡30፦ "ኡሪምና ቱሚም"፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡29፦ "ስለ ሙታን መጠመቅ" የሚሉና የመሳሰሉ የመጀመሪያ ትርጉሞች አሁንም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። እነዚህ ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር ትርጉ ማቸውን በትክክል ሊገልጥ የማይቻለው ናቸው። በአብዛኛው ግን የትርጓሜ መርሆችን በመጠቀም የመጀመሪያውን ትርጉም ለማወቅና በዚያው መሠረት ፍቺ ለመስጠት እንችላለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ክፍሎች ትርጉም በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ከሚገነዘቡት በላይ ይሆን እንደነበርም እንረዳለን። እግዚአብሔር (በዘፍጥረት 3፡15 ላይ) ስለ ክርስቶስ መምጣት መጀመሪያ የተስፋ ቃል በተናገረበት ጊዜ የሴቲቱ ዘር ሰኮናና ("ተረከዝ"፥ በ1980 ዓ.ም. እትም) የእባቡን ራስ መቀጥቀጥ ሁለንተናዊ ጥቅም ማንም ሊረዳ አይችልም ነበር። ኢየሱስ ዘኪዮስን "የአብርሃም ልጅ" (ሉቃስ 19፡9)፥ ባለው ጊዜ የሰሙ ሰዎች በገላትያ 3፡7፥ 29 ላይ በተመለከተው መሠረት ሙሉ ትርጉሙን እምብዛም ሊረዱ አልቻሉ ይሆናል። ሙሉ ትርጉሙ በኋላ ይገለጥ ይሆናል፤ መነሻ ትርጉሙ ግን ምን ጊዜም ቀዳሚ ነው።

የቀድሞውን ባህላዊ ሁኔታ ማወቅ የሚረዳ መሆኑን የሚያሳየን ምሳሌ በ1ኛ ሳሙኤል 12፡17 ላይ ይገኛል። በስንዴ መከር ወቅት እግዚአብሔር ዝናብ እንዲሰጥ የሚለምን መሆኑን ሳሙኤል ራሱ

ይናገራል። በተለመደው መሠረት ግን ከሚያዝያ እስከ ጥቅምት ድረስ ምንም ዝናብ አልነበረም። የሰንዴ መከር ጊዜ ከሚያዝያ አጋማሽ እስከ ግንቦት አጋማሽ ነበር። ስለዚህ ሳሙኤል ለሕዝቡ ይናገር የነበረው ከጌታ ስለመሆኑ ይህ የእግዚአብሔር ኃይል ማረጋገጫ ነበር።

በማርቆስ 11፡12-14 (እንዲሁም ማቴ. 21፡18-19) ኢየሱስ በለሲቱን የረገመበት ሁኔታ ተመዝግቧል። ማርቆስ 11፡13 ኢየሱስ በለሲቱን የረገማት ምንም እንኳን የበለስ ማፍሪያ ወቅት ባይሆን፥ ፍሬ ስላልነበራት ነው የሚል ስለሚመስል እርግማኑን ተገቢ አያስመስለውም። ነገር ግን መልካም በለሶች ከማፍሪያቸው ወራት ውጪም ቢሆን የተወሰነ ፍሬ ስለሚኖራቸው ጥቂት ፍሬዎችን ከዛፍ መፈለጉ ትክክል ነበር። የፍሬዎቹ አለመገኘት የዛፉን ፍሬ አልባነት ገለጠ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አሰጣጥ ጊዜ የቀድሞው ሁኔታ ጠቃሚ መሆኑን መመልከቱ ቀላል ነው። ይህም የተለያዩ ጉዳዮችን ያጠቃልላል፦

1. *ታሪካዊ ሁኔታዎች ወይም ነገሮች።*

ዳንኤል 5፡7፥16፦ ዳንኤል "ሦስተኛ ገዥ" ሆኖ የተሾመበት ምክንያት፥ ቀድሞውኑ ብልጣሶርና አባቱ በአንድነት ይገዙ ስለነበረ ነው። መጀመሪያውኑ ሁለት ገዥዎች ነበሩ።

በማቴዎስ 2፡22 አርኬላዎስ ከአባቱ ከሄሮድስ ይልቅ ለኢየሱስ ሕይወት ታላቅ አስፈሪ ሰው እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል።

2. *መልክዓ ምድራዊ ሁኔታዎች ወይም ነገሮች።*

ዮሐንስ 4፡4፦ ሰማሪያ በይሁዳና በገሊላ መካከል ያለ ክልል በመሆኑ ኢየሱስ በዚያ ማለፍ ነበረበት።

ኢዮኤል 2፡23፦ ሁለት አበይት የዝናብ ወራት እንደነበሩ ይታወቃል። የፊተኛው እህል የሚዘራበት ክረምት ሲሆን፥ የኋለኛው ደግሞ ቡቃያውን ለፍሬ የሚያዘጋጀው ዝናብ ነው።

3. *ባህላዊ ሁኔታዎች ወይም ነገሮች (ማኅበራዊ፥ ሃይማኖታዊ ወይም ቁሳዊ)።*

ሉቃስ 9፡59፦ አባትን መቅበር የበኩር ልጅ ከባድ ኃላፊነት ሲሆን፥ አባት ያልሞተ እንደሆነም ለዓመታት የሚያስጠብቅ ኃላፊነት ነበር።

ዮሐንስ 13፡3-5፦ የእንግዶችን እግር ማጠብ የአገልጋይ ተግባር ስለነበረ፥ ከደቀ መዛሙርቱ ማንም ቢሆን እግር ለማጠብ የፈቀደ አይመስልም።

## የቀድሞውን ሁኔታ መማር

በቀድሞው ሁኔታ መሠረት ትርጓሜ ለመስጠት የቀደመውን ሁኔታ መማር ይኖርብናል። እንዴት ነው ያን እውቀት የምናገኘው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ጠቢባን *ሥራዎች*፥ ማለትም ከመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ ስለ መልክዓ ምድር ከተጻፉ መጻሕፍት፥ ከማብራሪያዎች... ወዘተ. አያሌ ጠቃሚ ነገሮች ልናገኝ እንችላለን። ከእነዚህ መጻሕፍት የሚያገኟቸውን ሁሉ ይጠቀሙባቸው። የማያገኙ ከሆነ አስፈላጊውን የመነሻ መረጃ ሁሉ ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማግኘት መቻልዎን ያስተውሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ዋነኛ ተርጓሚ መሆኑን ቀደም ሲል ካስተዋልነው መሠረታዊ መርህ ተረድተናል። ግልጥ ላልሆኑ ብዙ ምንባቦች (ክፍሎች) መጽሐፍ ቅዱስ መነሻ የሚሆን መረጃ ይሰጣል።

ይህን መረጃ እንዴት ሊማሩት ይችላሉ? ሊከተሏቸው የሚገቡ አንዳንድ እርምጃዎች እነሆ!

1. *መጽሐፍ ቅዱስን ይማሩት።* ያንብቡት፤ ያንብቡት፥ አሁንም ያንብቡት። መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉ በሙሉ ባወቁት ቁጥር፥ ለትርጓሜ አሰጣጥ የሚረዳዎ መነሻ ወይም ስለቀድሞው ሁኔታ መረጃ የሚያስጨብጥዎ የበለጠ እውቀት ያገኛሉ። ታሪካዊ መጻሕፍትን ያንብቡ። የብሉይ ኪዳን ታሪክ፥ ለራሱና ለአዲስ ኪዳን፥ መነሻ ነው። አሪት (የመጀመሪያዎቹ አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት)፥ ለተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ በተለይም ለአዲስ ኪዳን የሚሆን ብዙ ባህላዊ መነሻዎች አለው። የኋለኞቹ ምንባቦች የቀደሙትን ግልጥ ያደርጓቸው ይሆናል። በጥሞናና ተደጋጋሚ በሆነ ንባብ አማካይነት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለተጠቀሱት ሕዝቦች፥ ዘመንና ባህል እውቀት ሊያገኙ ይችላሉ።

2. *ሲያነቡ ማስታወሻ ይያዙ ወይም ይጻፉ።* ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች (ገጸ ባሕርያት)፥ ልማዶችና መልክዓ ምድራዊ ሁኔታዎች ዝርዝሮችን ይጻፉ። ያልተለመዱ ነገሮችን፥ እንግዳ ቃላትን...ወዘተ. ያስተውሉ። ከዚያም ትርጉማቸውን ፈልገው ይጻፉ። ማናቸውንም የመጽሐፍ ቅዱስ ማገናዘቢያ እውነታዎችም ይጨምሩ። ይህ አሠራርዎ በኋላ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ በሚሹበት ጊዜ በቀላሉ ለማገናዘብ ይረዳዎታል። ማስታወሻዎችን በቋሚነት መያዝ (መጻፍ)፥ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። የማስታወስ ችሎታዎን የሚያግዝ ከመሆኑም በላይ፥ በፈለጉ ጊዜ የሚጠቀሙበት የእውቀት ክምችት እንዲኖርዎ ይረዳዎታል።

3. *ከዋናው ጽሑፍ ግራና ቀኝ ወይም ግርጌ ማጣቀሻዎች ያሉት መጽሐፍ ቅዱስ ካለዎት በማጣቀሻዎቹ ይጠቀሙ።* ብዙ ጊዜ የአዲስ ኪዳን

ጥቅሶች የብሉይ ኪዳን ማጣቀሻዎች አሏቸው። ሙሴ እባብ መስቀሉን የሚናገረው ዮሐንስ 3፡14፥ ከብሉይ ኪዳን ዘኁልቁ 21፡9ን በግርጌ ማመላከቻው ጠቅሷል። ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስዎ ያሉት ማጣቀሻዎች የተሟሉ አይደሉም። ስለሆነም የራስዎን ማመላከቻዎች ያዘጋጁ። አንድ ጥቅስ በሚያነቡ ጊዜ ሌላ ከታወሰዎ፥ ትዝ ያለዎትን ጥቅስ በመጽሐፉ ግራና ቀኝ ባለው ባዶ ቦታ ላይ ይጻፉት።

4. *መጽሐፍ ቅዱስዎ ካርታ ካለው መልከዓ ምድራዊ ስፍራዎችን ለማመልከት ይጠቀሙበት።* ለምሳሌ፥ መጽሐፈ ኢያሱን እያነበቡ በመጽሐፉ የተጠቀሱትን ስፍራዎች ከካርታ ላይ ቢመለከቱ ለድል ያበቃውን እቅድ ይረዳሉ። ኢያሱ ምዕራፍ 9 ውስጥ ገባዖን የተባለውን ስፍራ ይመልከቱና ኢያሱ ከነበረበት ቦታ ጋር የነበረውን ግንኙነት ያገናዝቡ።

5. *ሌሎች መጻሕፍት ከተገኙ እነርሱንም ይጠቀሙባቸው።* ከነዚህ የመጀመሪያው መዝገበ ቃላት ነው። የቃላት ትርጉም መግለጫ በሚሰጥበት ጊዜ ብዙ ባህላዊ ጉዳዮች ይዘረዘራሉ። ከባህል ጋር ግንኙነት ያላቸውን አያሌ ቃላት ቀደም ሲል ተመልክተናቸዋል። ባህላዊ ጉዳዮች በትርጓሜ ላይ ተጽዕኖ አላቸው፤ የሚገልጧቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትና ማብራሪያዎች ይሆናሉ።

## የትርጓሜ መመሪያዎች ወይም የመርህ ነጥቦች

ስለ አንድ ምንባብ የቀድሞ ሁኔታ (መነሻ) መረጃ ካለዎት ስለ ትርጓሜው ለማሰብ ዝግጁ ነዎት። ቀጥሎ ያሉት ሦስት የመመሪያ ነጥቦች ለዚህ ይረዳሉ።

1. *በምንባቡ ውስጥ የማይታወቁ ወይም ግራ የሚያጋቡ ነጥቦችን በጥንቃቄ በመመልከት፥ መነሻቸውን ማወቅ እነሱን ለመረዳት እንዴት እንደሚያግዝ ያስተውሉ።*

2. *ምንባቡ በተጻፈበት በዚያ ዘመን ወይም በዚያ ሁኔታ ለነበሩ ሰዎች ምን ይናገር እንደነበር ያጢኑ።*

3. *ላለንበት ባህል ተስማሚ የሚሆን ትርጉም ይፈልጉና በተገቢ አኳኋን ይጠቀሙበት።*

እስቲ በመሳፍንት 13፡3-5፥ የጌታ መልአክ ለማኑሄ ሚስት የምትወልደው ልጅ "ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይሆናል" ያለውን ምሳሌ እንጠቀምበት። መልአኩ "ናዝራዊ" ሲል ምን ማለቱ ነበር? ማጣቀሻ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ያለጥርጥር

ዘኁልቁ 6ን ያመለክታል። ማጣቀሻ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ከሌለዎ ግን፥ ቃሉን በአጭሩ አብራርቶ ለሙሉ ገለጣው ዘኁልቁ 6ን ከሚያመለክትዎ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት እርዳታ ሊያገኙ ይችላሉ። "ናዝራዊ"፥ ራሱን ለጌታ (ለእግዚአብሔር) ለመለየት ወይም ለማስረከብ ልዩ ቃለ-መሐላ የሚያደርግ መሆኑን ከዘኁልቁ መጽሐፍ እንማራለን። መሐላውን በሚፈጽምበት ጊዜ በተራ ሕይወት ከተለመዱ ሦስት ድርጊቶች መጠበቅ ወይም መገለል አለበት። የወይን ጠጅ ከመጠጣት ወይም ከወይን ጋር ግንኙነት ያለውን ነገር ከመብላት፥ ጸጉሩን ከመላጨትና የሰው በድን (ሬሳ) ከመንካት ይጠበቃል።

ይህ ቁም ነገር በግልጥ የሚያመለክተው፥ አንድ ሰው ለተወሰነ ዓላማ ወይም ሥራ ራሱን ለጌታ ለማስረከብ ሲፈልግና ለዚህም ቃለ መሐላ ሲያደርግ፥ ከዚያ በፊት ከሚፈጽማቸው አንዳንድ ነገሮች በመታቀብ ራሱን የሚለይ መሆኑን ነው። ወይን በፍልስጥኤም ምድር ዋና ሰብል ሲሆን ለእስራኤላውያን ዋናው የምግብና መጠጥ መገኛ ነበር። ጸጉርን መላጨት በወንዶች ዘንድ የተለመደ ይመስላል። ለዚህ ነው አለመላጨት የመለየት ምልክት የሆነው። ሬሳ ለቀብር ሲዘጋጅ መነካቱ የተለመደ ነበር። ነገር ግን ዘኁልቁ 19 ላይ እስከሬን የነካ ሰው በኋላ ከርኩሰት መንጻት እንዳለበት የሚያመለክት ሲሆን፥ ካህናት ሚቹ በጣም የቅርብ ዘመዳቸው ካልሆነ በጭራሽ ሬሳ እንደማይነኩ ዘሌዋውያን 21 ያስተምራል። ናዝራዊ የሆነ ሰው ግን ከነዚህ ድርጊቶች ፍጹም መጠበቅ አለበት። ከሌሎቹ ይልቅ እነዚህ ድርጊቶች ስለተከለከሉበት ምክንያት የተገለጠ ነገር የለም። ሆኖም ናዝራዊ በሌሎች የተለመዱ ክንውኖች ለመሳተፍ ነጻ ነበር።

እንግዲህ በዚያን ዘመን ለነበሩ ሰዎች፥ ትምህርቱ አንድ ሰው ራሱን በልዩ ሁኔታ ለጌታ ለማስረከብ ቃለ መሐላ እንደሚያደርግና ይህንንም በሚፈጽምበት ጊዜ ራሱን ከአንዳንድ ድርጊቶችና ኃላፊነቶች መጠበቅ የሚገባው መሆኑን የሚያስረዳ ነበር። ይህ ነበር ሳምሶን ከተወለደ ጀምሮ የተጣለበት ኃላፊነት። ያኔ ቃለ መሐላውን ስለ እርሱ ሆነው የፈጸሙት ወላጆቹ መሆናቸው ግልጥ ነው።

ይህን ጉዳይ በተግባር ለመተርጎም ብንመኝ፥ እንዴት ማድረግ እንደሚኖርብን የሚያስረዳ ግልጥ መግለጫ ወይም መመሪያ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አናገኝም። እንደውም ስለ ናዝራዊነት የተጠቀሰ ነገር የለም። ስለሆነም መመሪያውን በብሉይ ኪዳን እንደተገለጠው ነው በተግባር ልናውለው የሚገባ። አንድ ክርስቲያን ዛሬ ራሱን ለተለየ ዓላማ ለጌታ ለማስረከብ ይፈልግ ይሆናል። ቃለ መሐላ ሊያደርግና ራሱንም ከአንዳንድ ድርጊቶች ሊጠብቅ ይችላል። ምናልባት በዘኁልቁ 6 ላይ የተገለጡት

ክንውኖች ከሱ ድርጊትና እቅድ ጋር ተዛማጅነት አይኖራቸው ይሆናል። ቢሆንም ለመለየቱ ምልክቶች የእግዚአብሔርን ምሪት መጠየቅ፥ ስለ ጉዳዩም ከመንፈሳዊ መሪዎች ምክር መሻት ያስፈልገው ይሆናል። ነገር ግን እንዲህ ላለው ጉዳይ ተዘርዝሮ የተቀመጠለት ምንም ሕጋዊ መመዘኛ የለም።

በቀደሙ ሁኔታዎች መነሻነት ትርጓሜ ለመስጠት በሚፈለግበት ጊዜ ይህን የመሰለው አቀራረብ መልካም ነው። ታሪኩ በሚጠናበት፥ ትርጉሙን በዚያ ዘመን ሁኔታ መሠረት ለመረዳት በሚሞከርበት ወይም በተግባር በሚተረጎምበት ጊዜ አያሌ ችግሮች የሚፈጥሩ ብዙ ምንባቦች ይገጥማሉ። ይሁን እንጂ ያሉትን ምንባቦችና መጽሐፍ ቅዱስን ይበልጥ ባጠኑ ቁጥር የበለጠ ብርሃን በአእምሮዎ ይበራል። የእግዚአብሔር ቃል እውቀትዎም ያድጋል።

ለተጨማሪ ጥናት፡- 1ኛ ነገሥት 13 (የቤቴል ጠቃሚነት ከይሁዳ ጋር ሲስተያይ )፤ 2ኛ ነገሥት 3፡11 (ውኃ ያፈስ የነበረው ኤልሳዕ)፤ 2ኛ ነገሥት 4፡1-7 (የሴትየዋ ሁኔታ)፤ ማቴዎስ 8፡4 (ለካህን ማሳየት)፤ የሐዋርያት ሥራ 15፡20፥ 29 (እነዚህ አስፈላጊ ነገሮች የቱን ያህል መሠረታዊ፥ ወይም ምን ያህል ከአይሁዶች ወግ ጋር የተዛመዱ ናቸው?)፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡1-16 (የሴትዮዋ መከናነብ ባህላዊ ጉዳይ አለበት?)፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡8 (የርሱ እስረኛ)።

# 12

# ቅዱስ ቃሉን በራሱ መተርጎም

ስድስተኛው መመሪያ ይህ ነው፡- እያንዳንዱን ምንባብ ወይም ክፍል በመጽሐፍ ቅዱሱ አጠቃላይ አስተምህሮ መሠረት ይተርጉሙት ወይም ፍቺ ይስጡት። በሌላ አነጋገር የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል በራሱ ቃል ይፍቱት። የቱንም ያህል ሌሎቹን መመሪያዎች ቢከተሉ የትርጓሜዎ ውጤት ሌላውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሚቃረን ከሆነ፥ አተረጓጎምዎ አጠያያቂ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ከራሱ ጋር አይቃረንም። ስለ እግዚአብሔር አንድ መልእክት የሚሰጥ መሠረታዊና አንድ ወጥ መገለጥ ነው።

አንድ ጥቅስ ወይም ምንባብ በአገባቡ (በአካባቢው ባሉት ጥቅሶች፥ አንቀጾችና ምዕራፎች) መሠረት መጠናት ያለበት መሆኑን ቀደም ሲል ተመልክተናል። ስድስተኛ የሆነው የዚህ መመሪያ ጠቀሜታ ለአንድ ምንባብ የመጨረሻ አገባቡ፥ መላው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑን ማስገንዘብ ነው። ስለ አንድ ጉዳይ ተገቢው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት የሚገኘው፥ ከጉዳዩ ጋር የሚዛመዱ ምንባቦችን ወይም ክፍሎችን በማጥናት ብቻ ነው። ከምንባቦቹ አንዳንዶቹን ብቻ የምናጠና ከሆንን፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጉዳዩ ያለውን ትምህርት ለመረዳት አንችልም።

ለምሳሌ እርስዎ በአንድ ጫካ ውስጥ ይጓዛሉ እንበል። በመንገድዎ ላይ ለመሻገር የሚያዳግት ወንዝ ይኖራል። ስለ አካባቢው የሚያውቁት ነገር ከሌለ ወንዙ ውስጥ በመግባት ለመሻገር ይሞክራሉ። ያው ወንዝ ከሩብ ኪሎ ሜትር በኋላ ወደ ቀኝ የሚታጠፍና ጉዞውን እንደገና ወደ መጀመሪያው አቅጣጫ የሚመልስ መሆኑን ካወቁ ግን በመታጠፊያው በኩል በመዞር በቀላሉ በደረቅ መሬት ሊሻገሩ ይችላሉ። መጠነኛ ጠቅላላ እውቀት ከታላቅ ችግር እንዲያውም ከአደጋ ያድንዎታል። ባጠቃላይ እውቀት ውስጥ ታላቅ ጠቀሜታ አለ።

ስለ ጠቅላላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚኖረን እውቀት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚሰጠው ትምህርት የተሳሳተ እውቀት እንዳይኖረን ያደርጋል። ለምሳሌ በኤፌሶን 3፡14 ላይ፡- “ስለዚህ ምክንያት ...ከአብ ፊት እንበረከካለሁ” የሚል ቃል እናነባለን። እንግዲህ ጳውሎስ ለጸሎት የሚንበረከክ ከሆነ፥ እኛም በጸሎት ጊዜ መንበርከክ ያለብን መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል ብለን እንደመድም ይሆናል። ይህ አስተሳሰብ መቆም ወይም በደረት ተኝቶ መጸለይ ተገቢ መሆኑን የሚያመለክቱ

ምንባቦችን፥ እንዲሁም እግዚአብሔርን የሚያስደስተው የሰውነት አኳኋን ሳይሆን፥ የልብ ፍላጎት እንደሆነ የሚያስረዳ ቃሉን ችላ ማለት ነው።

ኑፋቄዎችና የሐሰት ትምህርቶች፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጣን ያላቸው የሚመስሉት፥ መምህራኑ በተወሰኑ ምንባቦች ብቻ በመጠቀም ሌሎችን ስለሚተዋቸው ነው። ከሐሰት ትምህርት እምነት ልንጠበቅ የምንችለው፥ ስለ አንድ ጥቅስ ያለንን ግንዛቤ ከመላው የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት ጋር በማገናዘብ ነው። ለአንድ ጥቅስ የመጨረሻና ቀኖናዊ መደምደሚያ ለመስጠት ከመቸኮል ልንጠነቀቅና ትሁት ዝንባሌ ሊኖረን ይገባል። ትርጓሜውን መስጠት ያለብን በመላው የእግዚአብሔር ቃል ብርሃንነት ነው።

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ትርጓሜ ሲሰጡ ወይም ማስተማር ሲጀምሩ፥ አንድን ክፍል ብቻ ይመለከታሉ። ለምሳሌ፥ በብሉይ ኪዳን በአንዳንድ ምግቦች ላይ የተሰጠውን ክልከላ ዛሬ ላለው የክርስትና ሥርዓት ወይም ጠባይ እንደ መነሻ ይወስዱታል። ወይም በአዲስ ኪዳን ያለውን የእግዚአብሔር ጽድቅ እግምት ውስጥ ሳያስገቡ፥ በብሉይ ኪዳን ሕግጋቱን የሚጠብቁ ሰዎችን ለመባረክ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ብቻ ያንጸባርቃሉ። ስለሆነም የብሉይ ኪዳን ሰዎች ለሕጉ በመታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ይሆኑ ነበር ብለው ይደመድማሉ።

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ከሚሆንባቸው ጉዳዮች አንዱ ስለ ሰንበት የምንሰጠው ትርጉም ነው። ሰባተኛው ቀን የዕረፍት ዕለት የመሆኑ ጉዳይ በብሉይ ኪዳን በጣም ግልጥ ተደርጓል። ይሁን እንጂ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፥ በተለይም ትምህርቱ ለጊዜያችን ያለውን ትርጉም ለመረዳት ሁለቱንም ማለት፥ ብሉይና አዲስ ኪዳናትን በአንድ ላይ ማጤን አለብን። በተጨማሪም የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቃል ኪዳኖችን፥ እንዲሁም የክርስቶስን ትንሣኤ ትርጉምና፥ የቀድሞይቱን ቤተ ክርስቲያን ልምድ ወይም አሠራር መመርመር አለብን።

ይህ መሆን ሲገባው፥ አንዳንድ ሰዎች ከአዲስ ኪዳን ብቻ በመውሰድ ብሉይን ይተውታል። አዲስ ኪዳንን ለመረዳት ይቻላቸው ዘንድ ብሉይ ኪዳንን ቢያነቡም፥ ክርስቲያኖች ሊያውቁት የሚገባቸውን እውነት በሙሉ ለመማር አዲስ ኪዳን ብቻውን በቂ እንደሆነ ይገምታሉ። የብሉይንና የአዲስ ኪዳንን ግንኙነት በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ 21 ላይ እንመለከታለን። እዚህ ማመልከት የምንፈልገው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መገለጥ መሆኑንና እያንዳንዱ ክፍልም መጠናት ያለበት በመጽሐፉ ሙሉ ብርሃን መሆን ነው።

መመሪያው ችላ የሚባልበት ሌላ መንገድ አሁንም ጥቂት እውነቶችን ከወንጌል ወይም ከሐዋርያት ሥራ በመውሰድ ተዛማጅ የሆኑትን የመልእክቶች ትምህርት መተው ነው። አንዳንድ ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ስለመጠመቅ የሚያስረዳ ትምህርታቸውን በአብዛኛው ከሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይወስዳሉ። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጠቃሚ እውነት ነው። እርሱን በግልጥ ለመረዳት የሚቻለው ደግሞ መላውን የአዲስ ኪዳን ትምህርት በማጥናት ብቻ ይሆናል።

## ተመሳሳይ ምንባቦች (ክፍሎች)

የመላውን መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የማግኛ አንዱ መንገድ ተመሳሳይ ምንባቦች የሚባሉትን ማጥናት ሲሆን፥ እነርሱም አንድ ዓይነት ጉዳይ የሚያነሡና በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚገኙ ጥቅሶች ናቸው። ለምሳሌ አንዳንዶቹን የኢየሱስ አባባሎችና ሁነቶች በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ወንጌሎች ተመዝግበው እናገኛቸዋለን። በመጽሐፈ ሳሙኤልና በመጽሐፈ ነገሥት ያለው ታሪክ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካለው ጋር በከፊል ተመሳሳይ ነው። ይህን ያህል የተቀራረበ ባይሆንም፥ የኤፌሶንና የቈላስይስ እንዲሁም የሮሜና የገላትያ መልእክቶች፥ አንዳንድ ክፍሎች ተመሳሳይ ናቸው።

ተመሳሳይ ምንባቦችን ሲመለከቱ ቀጥሎ ያሉትን የመርህ ነጥቦች በአእምሮዎ ይያዙ:-

1. *ተመሳሳይነቱ እውነተኛ ስለመሆኑ እርግጠኛ ይሁኑ።* አንድ ቃል በሁለት ጥቅሶች ውስጥ ቢገኝም ተመሳሳይ ትርጓሜ አይኖረው ይሆናል። (በኢሳ. 28፡6 እና 30፡2፥ 3 ላይ "ኃይል" የሚለውን ቃል ይመልከቱ።) ቃሉ አንድ ትርጉም ይሰጥ ዘንድ ግልጥ የአሳብ ተመሳሳይነት ሊኖር ይገባል።

2. *ልዩነቶችንና ተመሳሳይነቶችን፥ በጥንቃቄ ያስተውሉ።* በግልጥ ያዩዋቸው ዘንድ በማስታወሻ ይጻፏቸው። እያንዳንዱ ልዩነት ትርጉሙን እንዴት እንደሚለውጠው ልብ እያሉ ጥቅሱን በአገባቡ መሠረት ያጥኑት።

በማቴዎስ 10፡34 ኢየሱስ እንዲህ ይላል:- "ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ"። ይህ ቃል በቃል መወሰድ አለበት? አገባቡን በምናጠናበት ጊዜ "ጠላቶች" (ቁ. 36) የሚል ቃል ተጠቅሶ አይተናል። አባባሉ ጸብ ወይም ፍልሚያ ይመስላል።

ሉቃስ 12፥51 ከላይ የተጠቀሰው ምንባብ ተመሳሳይ ነው። ፍጹም ባይሆንም ዓረፍተ ነገሩም እጅግ ተመሳሳይነት አለው። "ሰይፍ" የሚለው ቃል "መለያየት" በሚለው ተለውጧል። ሁለቱ ምንባቦች የፈረሰ ትዳርና የተበተነ ቤተሰብን በተለያየ ገለጣ ያሳዩናል። ስለዚህ ምንባቦቹ ተመሳሳይ አገባብ ስላላቸው አሳባቸው ተመሳሳይ ነው። ሰይፍ የጸብ ተምሳሌት ነው። ስለሆነም ትርጉሙ መከፋፈል ይሆናል። ስለዚህ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ ያለው ጥቅስ ትርጉም በትክክል በሰይፍ ስለመጠቀም መሆን ያለመሆኑን ልንጠይቅ እንችላለን። ማቴዎስ 10፥37-38ን ስናነብ በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ የመጀመሪያውን ስፍራ መያዝ ያለበት ማነው? የሚለውን ጥያቄ እናነሣለን። አንድ ሰው በሕይወቱ ክርስቶስን የመጀመሪያ ካደረገ በእርሱና በቤተሰቡ መካከል ዘወትር መለያየት ይኖራል።

ዘወትር ተመሳሳይ ምንባቦች ስለማይገጥሙን ከላይ የተጠቀሱት መመሪያዎች የአገባብ መመሪያዎችን ያህል ጠቃሚዎች አይደሉም። ቢሆንም ተጨማሪ ምሳሌዎችን ማጥናቱ ይጠቅማል።

(1) 1ኛ ቆሮንቶስ 8፥6 እና ቈላስይስ 1፥16ን ያነጻጽሩ። አንዳንዶች ቈላስይስ 1፥16 ስለ አዲሱ መንፈሳዊ ፍጥረት የሚናገር እንደሆነ አድርገው ይወስዱታል።

(2) አንድ ሰው በኢሳይያስ 9፥6-7 ላይ (በ1980 ዓ.ም. እትም) ለመሢሑ የተሰጡትን አምስት ስሞች፥ በ1ኛ ሳሙኤል 17፥40 ላይ ዳዊት ከተጠቀመባቸው አምስት ድንጋዮች ጋር አዛምዷል። በእያንዳንዱ ክፍል "አምስት" የሚለውን ቃል ልብ ይበሉ። የሚያገናኛቸው ነገር አለ?

## መላውን መጽሐፍ ቅዱስ ማወቅ

የሚያጋጥመን የተግባር ጥያቄ የመላውን መጽሐፍ ቅዱስ እውቀት እንዴት ልናገኝ እንችላለን? የሚል ነው። መልሱን ለማግኘት አንዳንድ ነጥቦች እነሆ:-

1. *መጽሐፍ ቅዱስን በስፋትና በጥልቀት ያንብቡት።* በጥሞና ጊዜዎ ከሚያደርጉት አጭር ንባብ በተጨማሪ፥ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ የማንበቢያ ጊዜ እንዲኖርዎ ያቅዱ። መጽሐፍ ቅዱስን አንብበው ለመጨረስ አንድ ዓመት ይፈጅብዎ ይሆናል። ያም ቢሆን ጊዜና ጥረት ይጠይቃል። ለዓመታዊው ጥናት ቀላሉ መንገድ ወይም ስልት፥ በየዕለቱ ሦስት ምዕራፎችንና በየእሁዱ አምስት ምዕራፎችን ማንበብ ነው። ምዕራፎቹ ረጃጅምና አጫጭር ስለሆኑ ይህ ክፍል ለየዕለቱ ጥናት እኩል አይሆንም። ስለዚህ፥ ካሉት ብዙ አማራጮች አንድ ሌላ መምረጡ ያሻዎት

ይሆናል። በጥንቃቄ መመልከትና ማስታወሻዎችን መያዝ ምንባቦችን ለማስታወስ የሚያስችልዎ ከመሆኑም በላይ፥ ቀስ በቀስ የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል ከራሱ ቃል ጋር ማነጻጸርን ይማራሉ። በዚህ ዓይነቱ አሠራር ካልተጠቀሙ መጽሐፍ ቅዱስን የመማር እድገትዎ በጣም አዝጋሚ ይሆናል።

2. *መጽሐፍ ቅዱስን ያለማቋረጥ ያጥኑ።* ማንበብ ብቻውን በቂ አይደለም። ንባብና ጥናትዎን በማቀናጀት በየዕለቱ ጊዜ ሊመድቡለት ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስን እስኪጨርሱ ድረስ መጽሐፍ በመጽሐፍ የማጥናት ዕቅድ ይኖርዎት። "በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር" የሚለው መጽሐፍና ሌሎቹም ከተገኙ እንዲህ ላለው ጥናት ይረዱዎታል። እነዚህን የመሳሰሉ መርጃ መጻሕፍት ከተገኙ መላውን መጽሐፍ ቅዱስ በአራት ዓመታት ውስጥ ለመጨረስ ያስችላሉ። የየዕለቱ ጥናት፥ ሥራ ለሚበዛ ባቸው ሰዎች እንኳን በጣም ረጅም አይደለም።

መላውን መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ዓመታትም ቢሆን ለማወቅ እንደማይችሉ በማሰብ ምናልባት ተስፋ መቁረጥ ይሰማዎ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስን ከአሥርተ ዓመታት ጥናት በኋላ እንኳን፥ ሙሉ በሙሉ ለማወቅ የሚችል ሰው የለም። ሆኖም ሁልጊዜ በስልትና በጸሎት ማንበብ፥ እንዲሁም የማጥናትዎ ሂደት የእግዚአብሔር ቃል እውቀትዎ ያለማቋረጥ እያደገ መሆኑን ያረጋግጣል።

# 13

# ዘይቤያዊ አነጋገሮች

ሁሉንም ቋንቋዎች ለመተርጎም እንደ መርህ ከሚጠቀሙን መመሪያዎች በተጨማሪ፥ ልዩ የቋንቋ ዓይነቶች ልዩ መመሪያዎችን ይፈልጋሉ። በዚህ ክፍል አንዳንድ ልዩ የቋንቋ ዓይነቶችንና እነርሱን ለመረዳት የሚጠቅሙንን መመሪያዎች እናያለን። በቅድሚያም ዘይቤያዊ አነጋገሮችን እንመለከታለን።

*ዘይቤያዊ አነጋገር* [Figure of speech] አንድን ነገር ከቃል በቃል ወይም ቀጥተኛ ትርጉሙ ሌላ ፍች ለማስተላለፍ የምንጠቀምበት ቃል ወይም ሐረግ ነው። ሁላችንም እንዲህ ባለው አጠቃቀም አዘውትረን እንገለገላለን። ለምሳሌ ንግግር ከፍሬ ጋር  ምንም ግንኙነት ባይኖረውም "ፍሬ አልባ ንግግር" እንላለን። ይህን የምንለው ንግግሩ የሚረባ መልእክት ወይም ጭብጥ የሌለው መሆኑን ለመግለጥ ነው። ለ'እግዚአብሔር ቃል መቆም' እንደሚገባን ይነገረናል። ታዲያ አንድ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ማመን አለማመናችንን ሲጠይቀን በያለንበት መቆም አለብን ማለት ነው? አይደለም! ከላይ የተጠቀሰው ሐረግ የሚያስረዳን፥ በመመስከርና በማንኛውም አኳኋን እምነታችንን በድርጊት መግለጥ የሚገባን መሆኑን ነው። "በሣቅ ሞትኩ" ብዬ ብነግርዎ አያዝኑልኝም። ምክንያቱም አነጋገሬ ከሚገባ በላይ ተደነቅሁ ወይም ሣቅሁ ማለት እንጂ፥ ነፍስና ሥጋዬ ተለያይቶ ለሞት በቃሁ ማለቴ እንዳልሆነ ይረዳሉ።

ሰዎች በዘወትር ንግግራቸው የሚጠቀሙባቸው እነዚህ ዘይቤዎች ቃል በቃል ስሜታቸው እውነት ባይመስሉም፥ እውነት ናቸው። እውነትን ለየት ባለ፥ ይበልጥ ግልጥና ማራኪ በሆነ መንገድ በቀላሉ ያስረዳሉ። ትርጉሙን የምንቀበለው ገለጣው ዘይቤያዊ መሆኑን ለማሰብ ወይም የቃል በቃል ትርጉሙን ለማሰላሰል ጊዜ ሳንወስድ ነው። አእምሯችን ወዲያውኑ ይተረጉምልናልና።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ዘይቤያዊ አነጋገሮች መገንዘቡ አንዳንዴ ብዙም የማይገድ ሲሆን፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ በጣም አስፈላጊ ይሆናል። አንድ ጊዜ፥ ሁለቱ የቤተ ክርስቲያን የለውጥ መሪዎች፥ ማርቲን ሉተርና ኡልሪክ ዝዊንግሊ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ይወያዩ ነበር። የተነጋገሩትም ስለ ጌታ እራት ሲሆን፥ በተለይም "ይህ ሥጋዬ ነው" ስለሚሉት የክርስቶስ ቃላት ነበር። የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ይህን አባባል በቀጥታ ወይም ቃል በቃል በመውሰድ እንጀራውና ወይኑ በትክክል የክርስቶስ አካላዊ ሥጋና ደም ይሆናሉ ብላ አስተምራለች። ሉተርም

የካቶሊኮችን አመለካከት ያህል ርቆ ባይሄድም፥ የተጠቀሰውን የቃል በቃል አባባል አምኖ ነበር። ዝዊንግሊ ግን በጌታ ራት ጊዜ እንጀራውና ወይኑ የክርስቶስ ሥጋና ደም ተለዋጭ ናቸው፤ በዚያን ወቅት ክርስቶስ የሚገኘው በመንፈስ እንጂ በአካል አይደለም ሲል አጥብቆ ተከራከረ። ሁለቱ መሪዎች መግባባት ስላልቻሉ የተሐድሶ ለውጥ አራማጅ ቤተ ክርስቲያናት፥ በዚህ ጉዳይ የተነጣ ተከፋፈሉ። ስለዚህ የአንድ ቃል ወይም ሐረግ ትርጉም ዘይቤያዊ ወይም ቀጥተኛ የመሆኑ ጉዳይ አንዳንድ ጊዜ ወሳኝ ወይም አስፈላጊ ጥያቄ ነው።

## አነጻጻሪ ዘይቤዎች

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ዘይቤያዊ አነጋገሮች ይጠቀማል። ለነዚህ ዘይቤዎች በተለምዶ የተሰጧቸው ብዙ ስያሜዎች ስላሉ ቴክኒካዊ መጠሪያዎቹን ማወቁ መልካም ነው። በቅድሚያ ንጽጽርን የሚያመለክቱ ሁለት ዘይቤዎችን እንመለከታለን።

1. *ተለዋጭ ዘይቤ* [Metaphor/መታፈር]።* ተለዋጭ ዘይቤ በመሠረቱ በማይመሳሰሉ ሁለት ነገሮች መካከል ቃል በቃል ወይም በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ የተገለጠ ንጽጽር ነው። ለምሳሌ ውሻና ቀበሮን ሊያነጻጽሩ ቢፈልጉ፥ ሁለቱም እንስሳት ተመሳሳይ ስለሆኑ ተለዋጭ ዘይቤ አይኖርዎትም። ነገር ግን ሰውን ከዛፍ ጋር በማነጻጸር ተለዋጭ ዘይቤ ሊፈጥሩ ይችላሉ። የተለዋጭ ዘይቤ የተለመደ አቀማመጥ 'ሀ' ማለት 'ለ' ነው እንደማለት ይሆናል። በሌላ አባባል 'ሀ' እንደ 'ለ' ነው የሚል አገላለጥ ነው። ለምሳሌ፥ "እኔ ትል ነኝ"፥ "እርሱ አህያ ነው"፤ "እግዚአብሔር አለታችን ነው"።

ሌሎች ቅርጾችም አሉት፡- እነርሱም 'ለ' የ 'ሀ' ነው እንደማለት ዓይነት። "የደኅንነት ጽዋ" (ደኅንነት ጽዋ ነው ማለት ነው) እና "የርግማን እንጀራ" የሚሉት የሚጠቀሱ ምሳሌዎች ናቸው። ሌላው ቅርጽ "ይህ ሰው የሞተ ውሻ ነው" በማለት ፋንታ "ይህ የሞተ ውሻ" የሚለው ዓይነት ነው። ተለዋጭ ዘይቤ አንዳንዴ ድርጊትም ሊሆን ይችላል፡- "ደስታ መታጠቂያዬ ነው" በማለት ፋንታ "በደስታ አስታጠቀኝ" እንደማለት (መዝ. 30፡11)።

እነዚህ ሁሉ ተለዋጭ ዘይቤዎች በተለያዩ ሁለት ነገሮች መካከል አንድ የንጽጽር ነጥብ መኖሩን ያመለክታሉ። ከላይ የተጠቀሰውን የመጨረሻ ምሳሌ ይመልከቱ። ደስታ፥ ከመታጠቂያ ጋር እንዴት ተመሳሰለ? መታጠቂያ ለምን ያገለግላል? ልብስን ሰብስቦ በመያዝ ሰው

---
* አንድ ነገር በሌላ ተተክቶ የሚነገርበት ዘይቤ።

ለሥራ እንዲዘጋጅ ያደርጋል። መታጠቂያ ብርታትና መተማመን የመስጠት ሁኔታ አለው። በተመሳሳይ ሁኔታ ደስታ የመንፈስ ብርታትና መተማመንን ይሰጣል።

እነዚህን ጥቅሶች ይመልከቱና ስለ እያንዳንዱ ያስቡ፡- ኢያሱ 1፡8፤ 2ኛ ነገሥት 7፡2፤ ኢዮብ 13፡25፥ 41፡14፤ መዝሙር 109፡29፤ ኢሳይያስ 1፡31፥ 7፡4፤ ማቴዎስ 26፡26፤ ሉቃስ 11፡39፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-4፤ ኤፌሶን 1፡18።

2. *ተነጻጻሪ ዘይቤ* [Simile/ሲሚሊ]*፡ ተነጻጻሪ ዘይቤ ንጽጽሩ "እንደ" ወይም "ይመስል" ተብሎ ከመገለጡ በቀር በአብዛኛው ተለዋጭ ዘይቤን ይመስላል። "እኔ እንደ ትል ነኝ" ወይም "እግዚአብሔር ለኛ እንደ አለት ነው" ብንል ትርጉሙ ከላይ ከተጠቀሱት ተለዋጭ ዘይቤዎች ጋር አንድ ነው። ተነጻጻሪ ዘይቤ ይበልጥ ግልጥ ነው፤ ይሁንና አንዳንዴ ምናልባት በጣም ግልጥ ሳይሆን ይቀርና በቀላሉ የተሳሳተ መረዳት ውስጥ እንድንገባ ያደርጋል።

በኢዮብ 41፡24 (በ1980 ዓ.ም. እትም)፥ "ልቡ እንደ ወፍጮ ድንጋይ የጠነከረ" የሚለው አባባል ንጽጽርን ነው የሚያሳየው። በስፍራው የተጠቀሰው እያንዳንዱ ነገር ጠንካራ ቢሆንም፥ አንዱ አካላዊ ጥንካሬ ሲሆን ሌላው ግን አካላዊ አለመሆኑን እናውቃለን። ይህ በግልጥና በጎላ አኳኋን የልብን ደንዳናነት እውነት መግለጥ ሲሆን፥ በሌላ አባባል ግትርነትንና የዓላማን ብርታት የሚያመለክትም ሊሆን ይችላል።

ብዙዎቹ ተነጻጻሪ ዘይቤዎች ንጽጽርን በዚህ አኳኋን የሚያቀርቡ ቢሆኑም፥ አንዳንዶቹ ግን ሁለት ነገሮች ተመሳሳይ መሆናቸውን ብቻ በመንገር ተመሳሳይነታቸው በምንድነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ መሻቱን ግን ለኛ ይተውታል። ለምሳሌ ሚክያስ 7፡4፥ "ከእነርሱም ሁሉ የተሻለው እርሱ እንደ አሜከላ ነው" ይላል። በምን ሁኔታ ነው እንደ አሜካላ የሆነው? ይህን ምንባቡ በግልጥ ስለማይናገር፥ የንጽጽሩ ነጥብ (ፍሬ ሓሳብ) ምን እንደሆነ ለመረዳት ዓውደ ንባቡን ማጥናት ይኖርብናል።

ብዙ ጊዜ በተፈጥሮ ውስጥ ያሉ ነገሮች ለንጽጽር ያገለግላሉ። የአንድ ነገር አንዱ ባሕርዩ ለአንድ ነገር ማነጻጸሪያ ሲውል፥ ሌላ ባሕርዩ ደግሞ ለሌላ ማነጻጸሪያ ሊያገለግል ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የመልካምና የክፉ ልዩ ሁኔታዎች ተቃራኒ ማነጻጸሪያዎችን ይሰጣሉ። በሆሴዕ 6፡4፡- "ምሕረታችሁ...በማለዳም እንደሚያልፍ ጠል ነውና..." በሚለው ጥቅስ "ጠል" የሚለው ቃል የምሕረታቸውን ጊዜያዊነት ያመለክታል።

---

* አንድን ነገር ለማጉላትና ይበልጥ ግልጥ ለማድረግ ሲባል ከሌላ ነገር ጋር በማመሳሰል የሚገለጥበት ሁኔታ።

እንዲሁም እግዚአብሔር በሆሴዕ 14፡5፥ "ለእስራኤልም እንደጠል እሆነዋለሁ" ይላል። እናም ተከታዮቹ ቁጥሮች እግዚአብሔር የጠልን መልካም አገልግሎት፥ ማለት ለእጽዋት ሕይወትና እድገት መስጠቱን እንደገለጠ ያመለክታሉ። ስለዚህ በአንድ ክፍል ወይም ምንባብ የተጠቀሰው ልዩ ሁኔታ በሌላም ቦታ ተመሳሳይ ይሆናል ብለን መገመት የለብንም። እያንዳንዱን ተነጻጻሪ ዘይቤ መፍታት ያለብን በየራሱ ዓውደ ንባብ ሊሆን ይገባል። ("ርግብ" በሚለው ስም የሚጠቀሙትን የተለያዩ ተነጻጻሪ ዘይቤዎች ይመልከቱ፡- መዝ. 55፡6፤ ኢሳ. 59፡11፤ ኤር. 48፡28፤ ሆሴዕ 7፡11።)

ዓይነት ብቻ ሳይሆን የድርጊትንም ተነጻጻሪ ዘይቤዎች የሚያመለክቱ ክፍሎች እነሆ፡- መሳፍንት 7፡12፤ መዝሙር 59፡6፤ 92፡12፤ 133፡2-3፤ ምሳሌ 10፡26፤ ኢሳይያስ 9፡18-19፤ ኤርምያስ 17፡6፤ ማቴዎስ 17፡20፤ 25፡32-33፤ ሉቃስ 17፡24፤ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡2።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

ለዘይቤዎች ትርጓሜ ስንሰጥ እነዚህን ቅደም ተከተሎች ልንጠቀም እንችላለን፡-

ሀ. *የንጽጽሩ ነጥብ በጥቅሱ ወይም በአውደ ንባቡ የተመለከተ መሆኑን ያስተውሉ።* ተጠቅሶ ከሆነ፥ ያን ለትርጓሜው እንደ መክፈቻ ወይም ቁልፍ ይውሰዱት። ለምሳሌ በ1ኛ ነገሥት 12፡4፥ ሕዝቡ ሮብዓምን "አባትህ ቀንበር አክብዶብን ነበር" ይሉታል። ምን ማለታቸው እንደሆነ ከአገባቡ ነው ልንረዳ የምንችለው።

ለ. *የንጽጽሩ ነጥብ ካልተጠቀሰ፥ በመነጻጸር ላይ ያሉትን ነገሮች ይመልከቱና ተገቢውን ትርጉም ይውሰዱ።* ኢሳይያስ 1፡30፥ "...ውኃ እንደሌለባት አትክልት ትሆናላችሁና" ይላል። እንዲህ ያለው አትክልት በተለይም በበጋ ወቅት ምን ይሆናል? በእርግጥ ይደርቃል። ይህ የምስሉ እውነተኛ ትርጉም ሲሆን፥ የዓውደ ንባቡ ትርጉምም ጥፋትን ያረጋግጣል።

ሐ. *ትይዩ ወይም ተመሳሳይ ምንባቦችን (ካሉ) ይጠቀሙባቸው።* አንድ ነገር የተለያዩ ንጽጽሮችና ትርጉሞች እንደሚኖሩት በማስታወስ ጥንቃቄ ያድርጉ። በፍጹም እንግዳ ወደሆኑ ትርጓሜዎች እንዳያመሩ ከሚገባው በላይ በራስዎ ግምት አይጠቀሙ። ኢየሱስ በማቴዎስ 11፡29 ላይ፥ "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ" ይላል። ይህ በግልጥ ተለዋጭ ዘይቤ ነው። ግን ምን ማለት ነው? ድብቅ ትርጉሞችን ለማግኘት ስንል በግምት መመራት የለብንም። ዘፍጥረት 27፡40፤ ኢሳይያስ 47፡6 እና ኤርምያስ 27፡8፤ 28፡14 የሌላን ሰው ቀንበር መሸከምን በግልጥ አያመለክቱም?

## ተዛማጅ ዘይቤዎች

ከዚህ ቀጥሎ፥ አንድ ቃል ተዛማጁ ለሆነ ሌላ ቃል የሚተካበትን ሁኔታ የሚያሳዩ ሁለት ዘይቤያዊ አነጋገሮችን እንመለከታለን። እነርሱም ‘ሀ’ ተጠቅሶ ትርጉሙ ግን ‘ለ’ የሚሆንበት ሁኔታ ነው።

3. *ምትክ ስም [Metonymy/መታኒሚ]።* ይህ ዘይቤ አንድ አሳብ የሚገለጥበት ወይም ተዛማጅ የሆነ ጉዳይ የሚመለከትበት ነው። ሁለቱ ቃላት እንደ ምክንያትና ውጤት ሊዛመዱ ይችላሉ። (“የዳዊት መክፈቻ ቁልፍ፥” ራእይ 3፡7፥ በሚለው ሐረግ “ቁልፍ” ሥልጣንን ይወክላል)፤ ይህ የአንድ የሚገለጥ ነገር ምልክት ነው። ቦታ ሰዎችን እንዲተካ ሲደረግ ደግሞ (“በይሁዳም ሁሉ . . . ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፤” ማቴ. 3፡5፥ በሚለው ዓረፍተ ነገር ውስጥ “ይሁዳ” የሚለው ስም በአካባቢው የነበሩትን ሕዝቦች ለማመልከት አገልግሏል)።

መመርመር የሚገባቸው ሌሎች ክፍሎች፡- ዘፍጥረት 49፡10፤ ዘዳግም 17፡6፤ ኢያሱ 10፡21፤ ምሳሌ 10፡21፤ ኤርምያስ 21፡7፥ 10፤ ሆሴዕ 1፡2፤ የሐዋርያት ሥራ 11፡23፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡21 (በ1954 ዓ.ም. እትም) ናቸው።

4. *ወካይ [Synecdoche/ሰነክደኪ]።* ይህ ዘይቤ አጠቃላዩን በተወሰነ፥ ወይም የተወሰነውን በአጠቃላዩ ለማመልከት ያገለግላል። አንድ ነገር ለብዙ፥ ወይም ብዙ ነገሮች በአንድ ተወክለው እንደማለት ነው። ዘፍጥረት 42፡38 ላይ፡- “. . .ሽምግልናዬን በኀዘን ወደ መቃብር ታወርዱታላችሁ” ይላል። በዚህ ስፍራ ተናጋሪው በአእምሮው ያለው ጉዳይ ሽምግልናው ብቻ ሳይሆን ሁለመናው ነው። ትርጉሙ፥ “ወደ መቃብር ታወርዱኛላችሁ- ትቀብሩኛላችሁ” የሚል ነው። እንዲሁ አንድ ነገር አጠቃላዩን ሊገልጥ ይችላል። ኤርምያስ 25፡29፥ “በምድር በሚኖሩ ሁሉ ላይ ሰይፍን እጠራለሁና” ይላል። አንዲት ሰይፍ ብቻ ማለት ነው? አይደለም፤ አንድ ሰይፍ ብዙዎችን ስለወከለ ነጠላ ቁጥር፥ ለብዙ ቁጥር አገልግሏል።

ለተጨማሪ ጥናት የሚከተሉትን ይመልከቱ፡- ኢያሱ 7፡1፥ 11፤ 1ኛ ሳሙኤል 14፡45፤ 2ኛ ሳሙኤል 16፡21፤ ኢዮብ 29፡11፤ ኢሳይያስ 2፡4፤ ማቴዎስ 6፡11፤ 12፡40 (ይህ አጠቃላዩ አንድን ክፍል የገለጠበት ሁኔታ ነው?)።

ከላይ ለተጠቀሱት ማለት ለምትክ ስምና ለወካይ አጠቃቀም ትርጓሜ ለመስጠት ቀጥሎ ባሉት ሁለት መመሪያ ነጥቦች ይጠቀሙ፡-

ሀ. *በጥንቃቄ ይመልከቱ።* ቀጥተኛው፥ ማለት ቃል በቃሉ ትርጉም ምንም ስሜት የማይሰጥ ወይም ግራ የሚያጋባ ነው? ኢሳይያስ 22፡22፡- "የዳዊትንም ቤት መክፈቻ በጫንቃው ላይ አኖራለሁ" ይላል። ይህን ቃል በቃል ትርጉሙ ስንመለከተው ስሜት አይሰጠንም። ይሁንና በዘይቤያዊ አነጋገርነቱ ሥልጣንና ታላቅነትን ያመለክታል።

ለ. *ዘይቤያዊ ትርጉሙን ለማግኘት በምንባቡ አገባብና ሁኔታ ይጠቀሙ።* ስለ "ምስክሮች አፍ" ዘዳግም 19፡15 ይናገራል። አገባቡ ሲጠና "አፍ" ምን ማለት ነው? የውክልና ትርጉሙ "መናገር፥ ምስክርነት መስጠት" ይሆናል።

## ሌሎች ዘይቤያዊ አነጋገሮች

5. *እንቶኔ ዘይቤ [Apostrophe/ኢፖስትሮፊ]።* በዚህ ዘይቤ አንድ ጸሐፊ የሌሉ ወይም ግምታዊ የሆኑ ነገሮችን ወይም ሰዎችን በቀጥታ ያመለክታል። እናም በጊዜው ለሚጠቀምበት ዓላማ ነገሮችን ሰዎች እንደሆኑ አድርጎ ያቀርባቸዋል። "...በታላላቅ ጫፎቹ ተመክቶ፥ እግዚአብሔር ... የመረጠውን ተራራ ስለምን በንቀት ይመለከታል?" (መዝ. 68፡16፥ በ1980 ዓ.ም. እትም)። መዝሙረኛው በዚህ ስፍራ ተራራው የሚሰማና የሚያስብ አስመስሎ እንዴት እንደሚናገር ያስተውሉ። "...መካን ሆይ፥ ዘምሪ" (ኢሳ. 54፡1) የሚለውም ሌላ ምሳሌ ነው። ጌታ የሚናገረው ለአንዲት ሴት ሳይሆን፥ ለአንድ ሕዝብ ወይም አገር መሆኑን አገባቡ ያሳያል። እንቶኔ ለአንድ ጽሑፍ ሕይወትና ጣዕም የሚሰጥ ሥዕላዊ ዘይቤ ነው። ትርጉሙ በሚገባ ግልጥ ነው፤ ትርጉሙ ቃል በቃል አለመሆኑንም አገባቡ ሁልጊዜ ስለሚያመለክት፥ እምብዛም የትርጓሜ ችግር አይፈጥርም።

ሌሎች ማገናዘቢያዎች የሚገኙባቸው ክፍሎች፡- 2ኛ ሳሙኤል 18፡33፤ 1ኛ ነገሥት 13፡2፤ ኢሳይያስ 14፡12፤ ኤርምያስ 22፡29፤ 47፡6፤ ሕዝቅኤል 37፡4 ናቸው። የብሉይ ኪዳን ነቢያት ይህን ዘይቤ በብዛት ተጠቅመውታል።

6. *ሰውኛ ዘይቤ [Personification]።* በዚህ ዘይቤ አንድ ጸሐፊ ሰው ስላልሆነ ወይም ሕይወት ስለሌለው ነገር ሰው እንደሆነ አድርጎ ይናገራል፤ ማለትም ባሕርያቱ ለሌሏቸው ነገሮች የሰውን ባሕርያት ያጎናጽፋቸዋል። ለምሳሌ መዝሙር 98፡8፡- "ወንዞችም በአንድነት በእጅ ያጨብጭቡ" ይላል። ጸሐፊው ወንዞች እጅ እንደሌላቸው ያውቃል፤ ይህን ውብ ዘይቤ የተጠቀመው እግዚአብሔር ባለበት፥ ተፈጥሮም የሚባረክ መሆኑን በድንቅ ሁኔታ ለመግለጥ ነበር።

ሰውኛ ዘይቤ ብዙ ጊዜ ከእንቶኔ ዘይቤ ጋር ይቀናጃል። ለምሳሌ ዘዳግም 32፥1 ውስጥ፦ "ሰማያት ሆይ፥ አድምጡ" የሚለውን ቃል እናነባለን። እንዲሁም "ሰማያት ሆይ፥ . . . ዘምሩ" የሚለውን በኢሳይያስ 44፥23 እንመለከታለን። ቀጥተኛ ወይም ቃል በቃል ትርጉሙ የማይቻልና ብዙ ጊዜም የማይታመን ይሆናል። በዘይቤ አማካይነት ግን ያለ ችግር ልንረዳው እንችላለን። ነገር ግን እንዴት ነው የምንፈታው? መዝሙር 19፥2፦ "ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች" ይላል። እንደ እውነቱ ከሆነ ቀኖች አይናገሩም። ነገር ግን ቁጥር 1 ላይ "ይናገራሉ" እና "ያወራል" የሚሉት ግሦች ተመሳሳይ ናቸው፤ መላውም የምዕራፉ ምንባብ፥ እግዚአብሔርንና የእጆቹን ሥራ ያሳያል ይላል። ስለዚህ ትርጓሜውን ግልጥ የሚያደርገው አገባቡ ነው።

ሌሎች ማገናዘቢያዎች፦ ኢያሱ 24፥27፤ መዝሙር 77፥16፤ 114፥3፤ ምሳሌ 1፥20፤ 6፥22፤ ኤርምያስ 14፥7፤ 46፥10፤ ማቴዎስ 6፥34፤ ያዕቆብ 1፥15 ናቸው።

7. *ግነት [Hyperbole/ሃይፐርቦሊ]።* ግነት፥ ለሚገለጠው ነገር ትኩረት ለመስጠት ሲባል ሆን ተብሎ የሚደረግ ነው። ጸሐፊውም ሆነ አንባቢው፥ ይህን ሆን ተብሎ የሚደረግ ግነት መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ያለዚያ አንባቢው፥ ጸሐፊውን ባታላይነት ወይም ሐቅን በግድየለሽነት በማቅረብ ይጠራጠረው ይሆናል። መዝሙረኛው፦ "የውኃ ፈሳሽ ከዓይኖቼ ፈሰሰ" (መዝ. 119፥136) ባለ ጊዜ፥ በቀጥታ ወይም ቃል በቃል መናገሩ አልነበረም። የወንዝ ውሃ ከዓይኖቹ አልፈሰሰም። ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግ ካለማክበራቸው የተነሣ ክፉኛ አዝኗል። ስለሆነም ይህ ዘይቤ የልቡን ስብራት ገለጠለት።

እንደገናም እግዚአብሔር፦ "በነፋስም የምትንቀሳቀስ የቅጠል ድምጽ ታሸብራቸዋለች" (ዘሌዋ. 26፥36) ሲል ቃሉ፥ በቀጥታ እንዲወሰድ አስቦ ነበር ብለን ለመገመት እንችላለን? ይልቁን ይህ የሚያሳየው በስደት የሚኖሩትን አሳዛኝ ሕይወት ነው፤ በፍርሃትና በአደጋ ውስጥ ይኖራሉ። ግነት በዓረፍተ ነገሩ ግልጥ ካልሆነ፥ ትርጉሙን በትክክል የሚያሳየው አገባቡ ነው።

በተጨማሪ ዘዳግም 1፥28፤ 1ኛ ነገሥት 1፥40፤ 2ኛ ሳሙኤል 1፥23፤ መዝሙር 119፥20፤ ኤርምያስ 19፥4፤ 23፥9፤ ዮሐንስ 21፥25ን ያንብቡ።

8. *መጠይቅ [Interrogation]።* ይህ ዘይቤ የሚያገለግለው አንድ መልስ ብቻ ሊኖረው የሚችል ልዩ ጥያቄ ለማቅረብ ነው። ለመጠይቁ የሚሰጠው መልስ ግልጥ ስለሚሆን ጸሐፊው መልሱን መስጠት አያሻውም። እግዚአብሔር በኤርምያስ 32፥27፦ "እነሆ፥ እኔ የሥጋ ለባሽ

ሁሉ አምላክ እግዚአብሔር ነኝ፤ በውኑ እኔን የሚያቅተኝ ነገር አለን?" ብሎ ይጠይቃል። ይህ ለሙግት የቀረበ ጥያቄ አይደለም። አንባቢው "የሚያቅትህ ነገር ይኖርም አይኖርም ይሆናል" ለማለት አይችልም። ብቸኛው መልስ "የሚያቅትህ የለም" የሚል ነው። ጥያቄው ኤርምያስ ራሱ በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 17 ላይ፥ "ከአንተም የሚያቅት ነገር የለም" የሚለውን ነው የሚናገረው። እግዚአብሔር ቁጥር 27 ላይ መግለጫ ሊሰጥ ይችል ነበር። ነገር ግን ፍሬ ሐሳቡ ይበልጥ ጠንከር ብሎ ወደ አንባቢው የሚመጣው ጥያቄ በማንሣት ነው። አንባቢው ራሱ ጥያቄውን በአእምሮው ውስጥ በመመለስ ነጥቡን ወይም የመልእክቱን ፍሬ ሐሳብ ማግኘት አለበት እንጂ፥ እግዚአብሔር ፍቺውን ሲናገር የሚያዳምጥ ብቻ መሆን የለበትም። ይህ ዘይቤ በአብዛኛው ለአመክንዮታዊ ገለጣ የሚያገለግልና ብዙ ጊዜ መልስ የማይሰጠው ጥያቄ የሚል ስያሜ ይሰጠዋል።

መጠይቅ ዘይቤ ለተለያዩ ዓላማዎችም ሊያገለግል ይችላል። አንዳንድ ጊዜ አንድ ነገር እንዲተኮርበት የሚጋብዝ ሲሆን፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድን ርእስ ያስተዋውቃል። ለምሳሌ መዝሙር 8፥4:- "ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው?" ኤርምያስ 23፥29 ደግሞ፥ "በውኑ ቃሌ እንደእሳት፥ ...አይደለችምን?" ይላል። ይህ ዘይቤ የትርጓሜ ችግር አይፈጥርም። ጥያቄውን ወደ ሐተታዊ አባባል በመቀየር ትርጕሙ ሊገለጥ ይችላል። ለምሳሌ ከላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ:- "ቃሌ እንደ እሳት ነው" ማለት ይቻላል። ሊጠኑ የሚገባቸው ሌሎች ጥቅሶች:- ኢዮብ 21፥22፤ ኤርምያስ 2፥11፤ 13፥23፤ 30፥6፤ አሞጽ 3፥3-4፤ አብድዩ 1፥5፤ ማቴዎስ 7፥16፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፥22 ናቸው።

9. ውስጠ ወይራ *[Irony/አይረኒ]*። ውስጠ ወይራ የመልእክቱን ትርጕም በተቃራኒ ስለሚገልጠው ከሌሎቹ ዘይቤዎች ይለያል። የሚያገለግለውም ለሚገልጠው ነገር አጽንኦት ለመስጠት ነው። እንደ ግነት ዘይቤ ሁሉ በውስጠ ወይራም ምንም የማታለል ጉዳይ እንደሌለ ለአድማጮቹ ግልጥ መሆን ይኖርበታል። ንግግር በዚህ ዘይቤ የሚገለጥ ከሆነ፥ የተናጋሪው ድምጽ ራሱ ዘይቤውን ይገልጠዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉን፥ ከቃል ይልቅ በጽሑፍ የሠፈሩ ቃላት ስለሆኑ፥ ውስጠ ወይራን በመገንዘቡ ረገድ ችግር ይገጥመን ይሆናል።

በ2ኛ ሳሙኤል 6፥20 የንጉሥ ዳዊት ሚስት:- "...የእስራኤል ንጉሥ... ምንኛ የተከበረ ነው" አለችው። የጥቅሱ ቀሪ ክፍል በግልጥ የሚያሳየው ሴትየዋ በትክክል የገለጠችው፥ ንጉሡ ራሱን ማዋረዱን ነበር። በ1ኛ ነገሥት 22፥15 ሐሰተኞቹ ነቢያት እንዳደረጉት ሁሉ፥ የጌታም ነቢይ በታሰበው ጦርነት ድል እንደሚገኝ ተንብይዋል። ሆኖም የቃሉ አገባብ

እንደሚያስረዳው፥ ወታደሮቹ መሸነፋቸውን ያውቅ ነበርና የተናገረው በውስጡ ወይራ ነው። ቁጥር 15 ውስጠ ወይራ ካልሆነ፥ ነቢዩ ዋሽቷል ማለት ነው።

አንዳንድ ምንባቦችን ውስጠ ወይራ ናቸው ብሎ መናገሩ ከባድ ቢሆንም፥ አብዛኞቹ ግን ግልፅ ናቸው። እርግጠኛ በማይሆኑበት ጊዜ ስለ ሁለቱም ሁኔታዎች (ቃሉ ውስጠ ወይራ ስለመሆኑ ወይም ስላለመሆኑ) በጥንቃቄ ያስቡ። አባባሉን ቃል በቃል የተሰጠ ገለጣ እንደሆነ አድርገው ይመልከቱና፥ ያ ትርጉም በአገባቡ መሠረት መልካም ፍቺ መስጠቱን ያጥኑ። ከዚያም እንደ ውስጠ ወይራ ያስቡት። ብዙ ጊዜ ምርጫው ግልፁ ይሆናል።

ሌሎች ማገናዘቢያዎች፡- ዘኁልቁ 24፡11፤ 1ኛ ነገሥት 18፡27፤ ኢዮብ 12፡2፤ 38፡21፤ ዘካርያስ 11፡13 (የከበረውን!)፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 4፡8፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 11፡19 ናቸው።

የሚከሠቱት አልፎ አልፎ በመሆኑ የሌሎቹን ያህል ጠቃሚ ያልሆኑ ሦስት ዘይቤዎች አሉ። ከነዚህ አንዱ የሚያሰቅቅ፥ የሚከብድ ወይም ጸያፍ ነገርን በመልካምና በለዘበ ቃል የመግለጥ ዘይቤ ነው። ለምሳሌ በሐዋርያት ሥራ 7፡60 ላይ "ሞተ" በማለት ፋንታ "አንቀላፋ" ይላል። በመሳፍንት 19፡22 ላይ ደግሞ በግብረ ሰዶማዊ ድርጊት ፋንታ "እንድንደርስበት" በማለት ይጠቀማል። ሌላው ዘይቤ የአንድን ነገር ተጻራሪ በመተው በተለየ ሁኔታው መግለጥ ነው። ለምሳሌ፥ "ቅርብ ነው" ለማለት "ሩቅ አይደለም" እንላለን። በመዝሙር 51፡17 ላይ እንደተገለጠው "እግዚአብሔር አይንቅም" ማለት "እግዚአብሔር ይቀበላል" ማለት ነው። በ1ኛ ሳሙኤል 26፡8፡- "ሁለተኛም አልደግምም" ማለት "በአንድ ምት እገድለዋለሁ" ማለት ነው። ሦስተኛው ዘይቤ አስፈላጊ ያልሆኑ፥ ወይም ተደጋጋሚ ቃላትን መጠቀም ሲሆን፥ በ2ኛ ሳሙኤል 7፡22 ላይ "በጆሮአችንም እንደሰማን" ወይም በዘዳግም 3፡27 "በዓይኖችህ ተመልከት" የሚለውን ይመስላል። (በ1980 ዓ.ም. በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ አስፈላጊ ያልሆኑ ቃላት ቀርተዋል።)

ዘይቤያዊ አነጋገሮች፥ ለቋንቋ ውበትን፥ ግልፀኝነትንና አጽንኦትን ይጨምሩለታል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ዘይቤዎች ልንገነዘባቸውና ልንፈታቸው ከቻልን፥ የእግዚአብሔር ቃል በይበልጥ ይገለጥልናል። እንደውም ዘይቤዎችን በሚገባ ለይቶ መገንዘቡ፥ የሚቃረኑ የሚመስሉ ጥቅሶችን ለመረዳት ሊጠቅመን ይችላል። የእግዚአብሔር ቃል የትርጓሜ ባለጠጋ ነው። ትርጓሜውን ለመረዳት ስለሚያግዙን ስለነዚህ ዘይቤዎች ያመስግኑት።

# 14

# ተምሳሌቶች [Symbols]

በአንድ በተለመደ ትርጉም ላይ ግልጥነትን ለመጨመርና ይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ የሚያገለግለንን ማንኛውንም ነገር፥ ምልክት ወይም ተምሳሌት ልንለው እንችላለን። ይህም ተፈጥሯዊ የሆነ ነገር ማለት እንደ እርግብ፥ ወይም የተሠራ ነገር እንደ መስቀል ያለ ሊሆን ይችላል። ምልክቶቹን ወይም ተምሳሌቱን በተለምዶ ሕይወታችን እንገለገባልቸዋለን። ሰዎች ያገኙትን ውጤት ወይም ድል ለማሳየት በደረታቸው ወይም በትከሻቸው ላይ ምልክቶችን ያደርጋሉ። አንድ ሰው ጸጉሩን የሚያበጥርበት ሁኔታ፥ የሚፈልገውን አዝማሚያ ያመለክት ይሆናል። ሰላዮችና የመንግሥት ወኪሎች በመሰሎቻቸው ብቻ የሚታወቁትን ልዩ ቃላት ይጠቀማሉ።

መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ በምልክቶች ይጠቀማል። ምልክቶቹ ተፈጥሯዊ ወይም ተአምራዊ ሊሆኑ ይችላሉ። በእውኑ ዓለም የሚኖሩ ወይም በራእይ የታዩ ነገሮች ሊሆኑም ይችላሉ። ቁሳቁሶች (ማለትም እንደ ጨው ወይም የሻማ መብራት ማኖሪያ ያሉ ነገሮች)፥ ድርጊቶች (ዳቦ እንደ መብላት ወይም በጣም ትንሽ ከተማ እንደመመሥረት ያሉ)፥ ሥርዓቶች (እንደ ጥምቀት ወይም እንደ ፋሲካ ያሉ)፥ ቁሳቁሶች (እንደ ነጭ የሐር ልብስ ያሉ)፥ ቁጥሮች፥ ቀለሞችና ስሞች (እንደ ሰዶምና እንደ ግብፅ ኢየሩሳሌምን ለማመልከት)፥ ብረቶች (እንደ ወርቅና እንደ ነሐስ ያሉ)፥ ጌጣጌጦች (እንደ ሉል ወይም እንደ እንቁ ያሉ)፥ ፍጥረታት (እንደ አንበሳ ወይም ርግብ ያሉ)፥ ወይም ሌሎች ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

ተምሳሌቶች እውነትን ለመግለጥ ወይም ለመሸሸግም ሊያገለግሉ ይችላሉ። የተፈጥሮን ግልጥ ነገር ብቻ እንጂ ተምሳሌታዊ ትርጉሙን ከማይረዱ ሰዎች እውነትን ይደብቃሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ተምሳሌቶችን የመረዳቱን ነገር ለአንባቢው ይተውለታል እንጂ ብዙ ጊዜ አያብራራም። በመሆኑም ያሉትን ተምሳሌቶች ችላ ሳንል፥ የሌሉትንም በአእምሯችን ሳንፈጥር፥ በጥንቃቄ ማጥናት ይኖርብናል። ተምሳሌቶች የእውነት መግለጫ መሣሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። በዚያው ልክ ካላስተዋልናቸው ከባድ ስሕተቶችን ልንፈጽምባቸው እንችላለን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተለዋጭ ዘይቤዎች ብዙ ጊዜ ምልክቶች ወይም ተምሳሌቶች ናቸው። ለምሳሌ፦ "ይህ ሥጋዬ ነው... ይህ ... ደሜ ነው" (ማር. 14፡22፥ 24)። በዚህ ስፍራ ተለዋጩን ዘይቤ በቀላሉ

እንገነዘባለን። በዚሁ መሠረት እንጀራው የክርስቶስ ሥጋ፥ ወይኑ ደግሞ የደሙ ተምሳሌት መሆኑ እውነት ነው። በአገባቡ መሠረት አንድ መሠረታዊ ትርጉም ግልጥ ነው። ይኸውም ክርስቶስ፥ በሞቱ አካሉ የተሰበረ፥ ደሙም የፈሰሰ ስለሆነ እኛም የሞቱን ተምሳሌት ለማመልከት እንጀራውን እንቆርሳለን፤ ወይኑንም እንቀዳለን። ሌላም ትርጉም አለ። ለምንድነው የምንበላውና የምንጠጣው? የእኛ መብላትና መጠጣት ተምሳሌታዊ ድርጊቶች መሆናቸውን እንደ ዮሐንስ 6፡32-35፥ 48-63፤ 7፡37-39 ያሉ ብዙ ክፍሎች ያመለክታሉ። የምን ተምሳሌቶች? ኢየሱስ ሥጋውን ስለመብላትና ደሙንም ስለመጠጣት የተናገራቸውን ቃላት ቃል በቃል ብንወስዳቸው ወይም ብንተረጉማቸው (ዮሐ. 6፡53)፥ የሚናገረው ስለ ሰው የሰው ሥጋ በላነት ወይም ጭራቅነት ይመስላል። ይህ እጅግ የከፋውና የወደቀው ኃጢአተኛ ሰው ድርጊት ነው። በመሆኑም ተምሳሌቶችን መገንዘብ ከአሳዛኝ ስሕተቶች ሊያድነን ይችላል።

ውኃ የመንጻት ብቻ ሳይሆን የጥፋትም ተምሳሌት እንደሆነ ሁሉ፥ አንድ ነገር ከአንድ በላይ ተምሳሌትነት ሊኖረው ይችላል። በአንድ ክፍል ያለ ተምሳሌት ትርጉም፥ በሁሉም ክፍሎች ያው ይሆናል ብለን መገመት የለብንም። "ቀይ" በተለምዶ የክርስቶስ ደምና የንስሐ ተምሳሌት እንደሆነ ይታሰባል። ነገር ግን ይህ ቃልና ከዚህ ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነው ሐምራዊና ሌሎች ተመሳሳይ ቀለማት የተጠቀሱባቸውን ጥቅሶች መመርመር ያስደንቃል። ይህ ቃል በኢሳይያስ 63፡2 ፍርድን፤ በኢሳይያስ 1፡18 ኃጢአትን፤ በምሳሌ 23፡31 ወይን ጠጅን፤ በማቴዎስ 16፡2 ሰማይን እንዲሁም በናሆም 2፡3 ጽኑ ኃያላንን ያመለክታል። ይህ ቀለም የክርስቶስ ሞት ተምሳሌት ስለመሆኑ አንድም ክፍል በተብራራ አኳኋን የሚገልጠው አይመስልም። ይህን ትርጉም የምንቀበለው ከሆነ፥ ያን ያደረግነው ያለምንም ግልጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ እንደሆነ በመገንዘብ፥ እርግጠኛ ባንሆንም ሊሆን እንደሚችል ቆጥረን እንያዘው። "እባብ" የምን ተምሳሌት ነው (ዮሐ. 3፡14፤ ራእይ 20፡2)?

## ተምሳሌታዊ ቁጥሮች

መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ቁጥሮችን በምልክት ወይም በተምሳሌትነት ይጠቀምባቸዋል። እጅግ የታወቀው ቁጥር "ሰባት" ነው። ይህ ቁጥር ተምሳሌታዊ መሆኑን የሚነገረን ጥቅስ የለም። ነገር ግን ቁጥሩ ያለባቸውን ጥቅሶች ስናጠና ከቃል በቃል ትርጉሙ ሌላ ተጨማሪ ፍቺ እንዳለው ይሰማናል። ይህ ቁጥር የሚገኝባቸው ጥቅሶች ከ600 በላይ ስለሆኑ ሁሉንም መመልከቱ ከባድ ነው። ሆኖም የሚከተሉትን ሊመለከቱ ይችላሉ፡- ዘፍጥረት 29፡18፤ 41፡2፥ 18፤ 50፡10፤ ዘጸአት 12፡15፤

25፡37፤ ዘሌዋውያን 4፡6፤ 26፡24፤ ዘኍልቁ 23፡1፤ ዘዳግም 28፡7፤ ኢያሱ 6፡4፤ ሩት 4፡15፤ መዝሙር 119፡164፤ ምሳሌ 24፡16፤ 26፡16፤ ዘካርያስ 4፡2፤ ማቴዎስ 12፡45፤ የሐዋርያት ሥራ 6፡3፤ እና ራእይ 1፡4። ሰባት ቁጥር ብዙ ጊዜ የሙሉነት፥ የፍጹምነትና የአጠቃላይነት ኃይል እንዳለው እነዚህ ጥቅሶች ያመለክታሉ። ይህ ተጨማሪ ትርጉም የማይገኝባቸው ብዙ ጥቅሶችም ስላሉ፥ ቁጥሩ የሚገኝበትን ሁኔታ ለየብቻ መመልከት አለብን።

በምልክት ወይም በተምሳሌትነት ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ቁጥሮች፡- "ሦስት" (ብዙ ጊዜ ከሥላሴ ጋር በመዛመድ፡- ዘኍልቁ 6፡24-27፤ ኢሳ. 6፡3፤ ማቴ. 28፡19፤ 2ኛ ቆሮ. 13፡14፤ ራእይ 4፡8)፤ "አራት" (ብዙ ጊዜ ከምድር ሙሉነት ወይም ከፍጥረተዓለም ጋር እየተገናኘ፡- ኤር. 49፡36፤ ሕዝ. 37፡9፤ ኢሳ. 11፡12 ፤ ሉቃስ 13፡29፤ ራእይ 7፡1)፤ "አሥራ ሁለት" (ብዙ ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሆኑ ቡድኖች ጋር ይዛመዳል፡- ዘፍጥ. 49፡28፤ ዘጸ. 28፡21፤ ኢያሱ 4፡9፤ ማቴ. 10፡1፤ ራእይ 21፡12፥14)፤ "አርባ" (ብዙ ጊዜ ፈተናን ወይም ፍርድን ያመለክታል፡- ዘፍጥ. 7፡4፤ ዘጸ. 24፡18፤ ዘኍልቁ 14፡34፤ ዘዳግም 8፡1-5፤ ማቴ. 4፡2)።

እነዚህ ቁጥሮችና ምናልባትም ሌሎች፥ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተምሳሌነት አገልግለው ይሆናል። ነገር ግን እያንዳንዳቸው የሚገኙበት ሁኔታ ሁሉ ተምሳሌታዊ እንደሆነ አድርገን ማሰብ የለብንም። ያለዚያ የኢዮብ ሰባት ወንዶች ልጆቹ ፍጹምነትን፥ ሦስቱ ሴቶች ልጆቹ ደግሞ መልኮታዊነትን ያመለክታሉ እንደ ማለት ይሆናል። ኢሳይያስ 6፡3 ላይ "ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ" የሚለው ቃል ሥላሴን ያመለክት ይሆናል። ግን ወላጆቹ ሙሴን የደበቁባቸው ሦስቱ ወራት (ሐዋ. 7፡20) ወይም ጳውሎስ ብርሃኑን ያጣባቸው ሦስቱ ቀናት (ሐዋ. 9፡9) ተምሳሌታዊ ትርጉምና ጠቀሜታ ያለው አይመስልም። ስለዚያ ጉዳይ ጠቃሚ አሳብ ካላገኘን በአንድ ምንባብ ውስጥ ተጨማሪ ትርጉም መፈለግ አይኖርብንም።

## የትርጓሜ መመሪያ ነጥቦች

ተምሳሌቶችን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ምሳሌዎች ስላሉ፥ እነሱን ለማየት የሚያገለግሉ አንዳንድ የመመሪያ ነጥቦችን መመልከቱ መልካም ነው፡-

1. *ተምሳሌቶች ወይም ምልክቶችን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ የሚፈታበትን መንገድ ያጥኑ።* 1ኛ ጴጥሮስ 5፡8 ውስጥ "አንበሳ" የሚለውንና በኢሳይያስ 55፡10-11 "ዝናብ" የሚለውን ቃል ያስተውሉ።

“ጠል” የሚለውን ቃል በሆሴዕ 6፡4፤ 14፡5 ውስጥ ተመልክተናል። ተነጻጻሪዎቹ እያንዳንዳቸው የተለያየ ተምሳሌታዊ ትርጉም አላቸው። የተጠቀሰው ተምሳሌት እንደ “ቀለም” ያለ አጠቃላይ ምልክት ከሆነ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የቱን ያህል አንድን ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ተምሳሌታዊ ትርጉም አስፍቶ እንደሚገልጥ ለመመልከት ይረዳዎ ዘንድ፥ የሚያገኟቸውን ማመሳከሪያ መጻሕፍት ወይም መዝገበ ቃላት የቻሉትን ያህል ያገላብጧቸው። ሲያጠኑ የሚያገኟቸውን ተምሳሌቶች ዝርዝር በማስታወሻዎ (በተለየ ማስታወሻዎ ውስጥ ሊሆን ይችላል) መያዝ ያስፈልግዎ ይሆናል።

2. *ተፈጥሯዊ ነገሮችን ሲያጠኑ ተፈጥሯዊ ባሕርያቸውን ልብ ይበሉ።* ተምሳሌታዊው ትርጉም በነዚህ ሁኔታዎች ይገኛል። ለምሳሌ፥ “በግ” ትህትናን፥ “ጨው” ያለመበላሸትን ያመለክታሉ፤ “እሳማ” ደግሞ ርኵሰትን ይገልጣል። የትኛው ዓይነት አገላለጥ ተምሳሌታዊውን ትርጉም እንደሚሰጥ በሚያጠኑት ክፍል ውስጥ ይመልከቱ።

3. *ዓውደንባቡን ያጥኑ።* የተምሳሌቶችን ትርጉም ለመወሰን ዓውደንባብ በዋናነት ይረዳል። ለምሳሌ ኤርምያስ 24፡1-3 ላይ ኤርምያስ በለስ ያለባቸው ሁለት ቅርጫቶች ማየቱን ይገልጣል። አንደኛው ቅርጫት ደጎና በለስ፥ ሌላው የተበላሸ መያዣቸውን ያመለክታል። ከቁጥር 4-10 ባለው ክፍል ተምሳሌቱ በሁለት ምድብ ያሉ ሰዎችን የሚያመለክት መሆኑን ጌታ ይገልጣል። ስደተኞቹ በመልካም በለስ ሲመሰሉ፥ ንጉሡና በከተማው የቀሩት ደግሞ በመጥፎ ወይም በተበላሸ በለስ ተመስለዋል።

4. *ከመጽሐፍ ቅዱስ ሳይሆን፥ ከራስዎ አእምሮ የሚመነጩ ግምቶችን ወይም በዘፈቀደ የሚሰጡ ትርጉሞችን ያስወግዱ።* እርስዎ ለሚያስቡት ትርጉም ትክክለኛ ማረጋገጫ የማያገኙ ከሆነ፥ ሊሉ የሚችሉት ትልቅ ነገር “ሊሆን የሚችል” ትርጉም ማለት እንጂ፥ እንደው በቀኖናዊነት “ትርጉሙ ይህ ነው” ለማለት አይችሉም።

ምናልባት ተምሳሌቶች የሚገኙባቸው አንዳንድ ጠቃሚ ክፍሎች፦ ዘጸአት 13፡21፤ መዝሙር 69፡2 ከኢሳይያስ 44፡3 ጋር፤ ሕዝቅኤል 1፡13 ከዕብራውያን 12፡29 ጋር፤ ሕዝቅኤል 37፡1-4፤ ሚክያስ 4፡13 ከመዝሙር 107፡16 ጋር፤ ማቴዎስ 17፡2 ከራእይ 19፡8 ጋር ናቸው።